«‹በጎውን ማን ያሳየናል?›› የሚሉ ብዙዎች ናቸው።››
መዝ.፬÷፮

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፩ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፱ ቤት አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፭ የሕፃናት ዓምድ

፲፯ ትዝብት

፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ

የቤት ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ


ጳጉሜን ፩ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል

newspaper@eotcmk.org

ምክትል ዋና አዘጋጅ

ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር

ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር

ምኒልክ ብርሃኑ

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና

ጸሐፊ

ገነት ታደሰ

# ሀገረ ስብከቱ መስለው ከሚያጠፉ ጠላቶች መጠንቀቅ እንደሚገባ አስጠነቀቀ

ካሳሁን ለምለሙ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ማሕበረ ምእመናንን መስለው እርሱን ከሚያጠፉ ጠላቶች መጠንቀቅ እንደሚገባው ባወጣው መግለጫ አስጠነቀቀ።

የሀገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታ መነሻ አድርገው ቤተ ክርስቲያንን ለማጥቃትና ምእመናንን ለመበተን የተነሡ ካሓዲ መናፍቃን መኖራቸውን ሀገረ ስብከቱ በመግለጫው አስታውቆ "ክህነት የለም፤ ካህናት ተወግዘዋል እንዲሁም መስቀል አትሳለሙ" በማለት ሕዝበ ክርስቲያኑን እያወዛገቡ እንደሆነም ጠቁሟል።

አያይዞም "የቤተ ክርስቲያንን መምህራን አትስሙ የዘንዶ መልእክተኞች ናቸው፤ ሃያ አራት ሃያ አራት እየሆናችሁ ፅዋ ጠጡ እንደ ሥጋወደሙ ይቆጠርላችኋል፤ ቴዎድሮስ እየመጣ ነው ተመዝገቡ፤ በሀገር ጥበቃ አትሳተፉ፤ ባንዴራ ስቀሉ፤ መታወቂያ አውጡ ከመቅሰፍት ትሠወራላችሁ በመርከብም ትሳፈራላችሁ፤ ዓለም ሊያልፍ ነው የምንተርፈው እኛ ብቻ ነን፤ የበረሃ አባቶች እንዲህ ብለዋል" የሚሉ የፈጠራ ወሬዎች ሕዝበ ክርስቲያኑን እያወዛገቡ መሆናቸውን ሀገረ ስብከቱ አስታውቋል።

በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን እንደረከሰች፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ከመጸለይ እቤት ሆኖ መጸለይ እንደሚገባ፣ ሲኖዶስም እንደተወገዘ፣ ክህነት መቀበል እንደማያስፈልግ፣ ሥጋወ ደሙ እንደሌለ፣ ቅዳሴ እንደማያርግና ቊርባን ትክክል እንዳልሆነ በመስበክ ራሱን "ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን" ብሎ የሰየመው የጥፋት ቡድን ምእመናንን እያደናገረ መሆኑን ሀገረ ስብከቱ አንሥቷል። መጠሪያ ስማቸውን "ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን" በማለት ህዝበ ክርስቲያኑን የሚያታልሉበት ስልት ነድፈው በተለያዩ የማኅበራዊ መገናኛ ዘዴዎች አማካይነትና በፅዋ ማኅበራት መልክ እየሠሩ በመሆናቸው ማንኛውም ኦርቶዶክሳዊ ምእመን ከእነርሱ ሰይጣናዊ አሠራር ራሱን ጠብቆ ሌሎችን እንዲጠብቅ ሀገረ ስብከቱ ጥሪ አቅርቧል።

እነርሱን የሚከተል ማንኛውም አማኝ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን እንዳልሆነ ያሳሰበው ሀገረ ስብከቱ የሰሙ ላልሰሙ፣ ያነበቡ ላላነበቡ በማድረስ ክርስቲያናዊ ድርሻን መወጣት እንደሚገባ ሀገረ ስብከቱ አሳስቧል።

ራሱን "ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን" ብሎ የሰየመው የመናፍቃንና የካሓድያን ስብስብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥቃት ምእመናንን ደግሞ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ለመንጠቅ ለበርካታ ዓመታት ዕቅድ ነድፎ ሲሠራ መቆየቱ ይታወሳል። ቤተ ክርስቲያንም በተለያዩ መድረኮች ለአገልጋዮቿና ለምእመናን የግንዛበቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን ስትሰጥ ቆይታለች፤እየሰጠችም ትገኛለች።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሕክምና ማኅበር የህክምና አገልግሎትና የመድኃኒት ድጋፍ ማድረጉን አስታወቀ

ካሳሁን ለምለሙ




ድጋፍ ያደረጉ የማኅበሩ አባላት በከፊል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሕክምና ማኅበር ከወሎና ከሰሜን ሸዋ ተፈናቅለው በደብረ ብርሃን ጊዜያዊ መጠለያ ለሚገኙ ተፈናቃዮች የሕክምና አገልግሎትና የመድኃይኒት ድጋፍ ማድረጉን የማኅበሩ አስተባባሪ ዶክተር ዘላለም መራሄ አስታወቁ።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተከሰተው ጦርነት ምክንያት በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በደብረ ብርሃን ጊዜያዊ መጠለያ እንደሚገኙ የገለጡት አስተባባሪው በስደተኞች ጣቢያ ውስጥ ከሁለት መቶ ዐሥር ሺህ በላይ ተፈናቃዮች መኖራቸውን አስረድተዋል። እነዚህ በአስከፊ አኗኗር ውስጥ የሚገኙ ተፈናቃዮች በመድኃይኒት እጥረት ምክንያት ለከፋ የጤና ችግር መጋለጣቸውንም አረጋግጠዋል።

አስተባባሪው አያይዘውም በልዩ ልዩ በሽታዎች ለሚሰቃዩ ወገኖች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሕክምና ማኅበር ኅዳር ፳፮ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በሃያ ስድስት የሕክምና ባለሙያዎች አማካይነት በጊዜያዊ መጠለያ ተገኝቶ ለወስጥ ደዌ፤ ለሕጻናት፤ ለጨጓራ፤ ለሥነ አዕምሮ፤ ለጥርስ እና ለፊዚዮ ቴራፒ ሕሙማን የሕክምና አገልግሎት መስጠቱንና የመድኃኒቶች ድጋፍ ማድረጉን አስታውቀዋል።

በመጨረሻም አስተባባሪው የህክምና ቡድኑ ለጤና ባለሙያዎች ሥልጠና መሥጠቱን ጠቁመው ለዞኑና ለደብረ ብርሃን ጤና ቢሮም ልዩ ልዩ መድኃኒቶችን ማበርከቱንና ማኅበሩ በቀጣይም የበኩሉን ለማድረግ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው ገልጠዋል።

# በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሠለጠኑት ሰባክያኑ ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ትልቅ ድርሻ እንደሚኖራቸው ተገለጠ፤

ምኒልክ ብርሃኑ



ዲ/ን ደስቂዮስ ሽብሩ

በሰባ ስድስት ቋንቋዎች የሠለጠኑት ሰባክያን ለስብከተ ወንጌልን መስፋፋት ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው የጽርሐ ጽዮን ዘተዋሕዶ አንድነት ኑሮ ማኅበር የካህናት ሥልጠና ማእከል ዋና ኃላፊ ዲ/ን ደቅስዮስ ሽበሩ ገለጡ፡፡

ኃላፊው ይህንን የገለጡት የአንድነት ኑሮ ማኅበሩ የተመሠረተበትን የ፴ኛ ዓመት በዓል እና የካህናት ማሠልጠኛ ማእከሉ ለ፳፬ ዓመታት ላከናወናቸው ተግባራት ዕውቅና ለመስጠት ኅዳር ፳፯/፳፻፲፬ ዓ.ም በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባዘጋጀው መድረክ ላይ ነው፡፡

ዲ/ን ደቅስዮስ በዕለቱ የማሠልጠኛ ማእከሉን የ፳፻፲፫ ዓ.ም የሥራ ዘገባ እና የ፳፻፲፬ ዓ.ም ዕቅድን ያቀረቡ ሲኾን፤ በዘገባቸውም የአንድነት ኑሮ ማኅበሩ የሰባክያነ ወንጌል ማሠልጠኛ ማእከል ከተቋቋመ ከ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፳፻፲፫ ዓ.ም ድረስ በክረምት እና በበጋ መርሐ ግብር ከ፶፪ አህጉረ ስብከት በ፸፮ ቋንቋዎች ቃለ እግዚአብሔርን ማስተማር የሚችሉ ፲፻፸፱ (አንድ ሺህ ሰባ ዘጠኝ) ደቀ መዛሙርትን አፍርቷል፡፡ለ፴፫ኛ ዙር ያሠለጠናቸውን ሰባክያነ ወንጌል በቅርቡ እንዳስመረቀ የጠቆሙት ኃላፊው ከሠልጣኝ ደቀ መዛሙርቱም መካከል ከሌሎች አፍሪካ ሀገራት የመጡ ደቀ መዛሙር እንደሚገኙም ተናግረዋል፡፡ ለዚህ ሁሉ ጥረት መሳካት በአሳብ፣ በገንዘብ እና በሞያ ድጋፍ ያደረጉ አካላትን አመስግነዋል፡፡

የሥልጠና ማእከሉ አቅሙን በማሳደግ በቀጣይ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ለሚመጡ ሰባክያነ ወንጌል ሥልጠና ለመስጠት ዝግጅቱን ማጠናቀቁን የገለጹት ዋና ኃላፊው በተጨማሪም አገልጋይ አጥተው እስከ መዘጋት ለደረሱ በገጠሪቱ አካባቢ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ለአንድ ዓመት የሚቆይ የዲቁና፣ የቅስና እንዲሁም ስብከተ ወንጌልን ማስተማር የሚችሉ አገልጋዮችን ማፍራት የሚያስችል ዕቅድ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንም አክለዋል፡፡ አያይዘውም የአንድነት ኑሮ ማኅበሩ እና የሥልጠና ማእከሉ ያዘጋጃቸውን የተለያዩ ፕሮጀክቶች ለማሳካት ከምእመናን በገንዘብ፣ በሞያ፣ በቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻም በምስጋና መርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ቃለ ምዕዳን የሰጡት የምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት የሆሮ ጉዱ ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል “ቤተ ክርስቲያን ልትሠራ የሚገባውን ከፍተኛ አደራ እና ኃላፊነት እንደራሳችሁ አድርጋችሁ በመውሰድ የወንጌል አገልግሎትን የሚያግዙ አገልጋዮችን ማፍራታችሁ መልካም ተግባር ነውና በ፴ ዓመታት ጉዞ ውስጥ በርካታ ፈተናዎችን አልፋችሁ እዚህ መድረሳችሁ የሚያስመሰግን ተግባር ነው፡፡ ክርስትና እና ፈተና የማይለያዩ በመሆናቸው ከዚህ የበለጠ ለመሥራት ምእመናንም ይህንን የተቀደሰ ዓላማ መደገፍ ይኖርባቸዋል” ሲሉ አሳስበዋል፡፡

የጽርሐ ጽዮን ዘተዋሕዶ አንድነት ኑሮ ማኅበር መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም ከቅዱስ ሲኖዶስ እና ከከተማ ልማትና ቤቶች ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዕውቅና ፈቃድ አግኝቶ ስብከተ ወንጌልን ለማፋፋት፣ የተቸገሩትንም ለመርዳት፣ ጎጂ ባህሎችን ለመቅረፍ ብሎም በልማት ሥራዎች ለመሳተፍ የተቋቋመ መንፈሳዊ ማኅበር ሲሆን ከ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ጀምሮ መለከት የተሰኘች መጽሔትን በማዘጋጀት ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት አስተዋፅኦ እያደረገ የሚገኝ ማኅበር እንደሆነ ይታወቃል፡፡

# ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ

በዓለማችን ላይ ብዙዎች የእግዚአብሔር ነቢያት ነን በማለት ተነሥተው በሕዝቡ መካከል የሐሰት ትንቢት በመናገርና በርካቶችን አስተው ከመንገድ እንዲወጡ ከሃይማኖታቸው ፈቀቅ እንዲሉ አድርገዋል። በዓለም ላይ የሚከሠቱ የተለያዩ ሁነቶችን መነሻ አድርገው ራሳቸውን ከእግዚአብሔር እንደተላከ መልእክተኛ በማስመሰል እግዚአብሔር ያላለውን እግዚአብሔር እንዲህ አለ እያሉ በሐሰት በመናገር ብዙዎችን የእነርሱ ተከታዮች እንዲሆኑ አድርገዋል። እንደ ነቢዩ ሙሴ፣ ነቢይት ዲቦራ ነቢዩ ናታን የመሳሰሉ ነቢያት ከእግዚአብሔር ተልከው እውነተኛውን ነገር ለሕዝቡ የሚናገሩ፣ የሚመክሩ፣ የሚያጽናኑ ነቢያት በሕዝቡ መካከል ነበሩ። በተቃራኒው እንደ በለአም ዓይይነቶቹ ደግሞ ከእግዚአብሔር ቃል ፈቀቅ ብለው እግዚአብሔር ያላለውን ያልተናገረውን ከእግዚአብሔር አለ በማለት እግዚአብሔርን ሕዝብ ለመርገም ተነሥተዋል።

በምድር ላይ እጅግ ሰፍቶና ተንሰራፍቶ የምናገኘው የሐሰተኞች ነቢያት ጉዳይ በየዘመናቱ መልኩን እየቀያየረ ዛሬ ላይ ደርሷል። ዛሬም እንደ ትላንትናው ሁሉ እግዚአብሔር እንዲህ ተናግሯል፣ እንዲህ እና እንዲህ ይሆናል የሚሉ በራስ ፈጠራ ላይ የተመሠረቱ ትንቢቶች በሕዝቡ መካከል በብዛት ይነገራሉ። እነዚህ የሀሰት ትንቢቶችም ዘመኑ ያመጣውን ቴክኖሎጂም በመጠቀም በአንድ ጊዜ ከዓለም ጫፍ እስከ ጫፍ ይደርሳሉ። የሰውን የነገ ተስፋ የሚያጨልሙ፣ በሰዎች መካከል ሽብርና አሉባልታን የሚነዙ፣ የሰዎችን አኗኗር የሚያዛቡ የሐሰተኞች ነቢያት ትንቢቶች በተለይ ባላተረጋጋ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ ቀላል አይደለም።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹ሐሰተኞች ነቢያት በሕዝቡ መካከል ነበሩ፤ እንዲሁም በመካከላቸው ሐሰተኛ አስተማሪዎች ይሆናሉ›› (፪ኛ ጴጥ.፪፥፩) እንዳለው እውነተኞቹን የቤተ ክርስቲያን መምህራንን ባሕታውያን በመምሰል ከእግዚአብሔር ያልተነገራቸውን ትንቢት እግዚአብሔር አለ በማለት የሚናገሩት የቤተ ክርስቲያን ሰዎች፣ በስመ ባሕታውያን የሚጠሩ መሆናቸው በቤተ ክርስቲያን እና በእምነቱ ውስጥ ያሉ ምእመናን ላይ የሚያደርሱት ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ተሰግስገው ያሉት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመሆኑ የሚያስተምሩትም ሆነ የሐሰት ትንቢት የሚናገሩት በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ላይ ነው። ደግሞ ጉዳዩን እጅግ አሳሳቢ አድርጎታል። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያንን መለያ መስቀል መያዛቸው፣ የቤተ ክርስቲያንን ልብሰ ተክህኖ መልበሳቸው እና የምንኩስና ቆብ መድፋታቸው በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ እንዲታመኑ አድርጓቸዋልና።

እግዚአብሔር እንዲናገሩ ያዘዛቸውን የሚናገሩ፣ ሕዝቡን፣ ነገሥታቱን የሚገሥፁ፣ የሚመክሩ፣ የሚያስጠነቅቁ ፣ የሚያስተምሩ ቅዱሳን አባቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዛሬም እንዳሉ ይታመናል። ሆኖም ከዚህ በተቃራኒ የራሳቸውን ሥጋዊ ፍላጎት ለማርካት እና ተከታይ ምእመናንን ለማፍራት የሚባዝኑት ትንሽ አይደሉምና ጉዳዩ ቸል የሚባል አይደለም። በተለይ በንግሥ እና በሰንበት ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን በቅርብ ርቀት ላይ ቆመው ሰንሰለት ታጥቀውና ቆዳ ለብሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደውን ሕዝብ ከመንገድ አስቀርተው ያልተነገራቸውንና ያልታዘዙትን በምእመኑ ላይ የሚጭኑ ባሕታውያን ነን ባይ የሐሰት ትንቢት ተናጋሪዎችን ሃይ የሚላቸው ማን ይሆን? ችግሩ እጅግ የገዘፈ ነውና በጊዜ መላ ሊፈለግለት ይገባል።

በዐደባባይ በቤተ ክርስቲያን ስም ከሚደረገው ማጭበርበር ባሻገር ዘመኑ ባፈራው ቴክኖሎጂ ተጠቅመው በየማኅበራዊ ሚዲያው ብቅ እያሉ እንዲህ ‹‹ዓይነት መቅሰፍት በሀገሪቱ ላይ ይመጣል››፣ ‹‹እግዚአብሔር ስለ እከሌ እንዲህ እና እንዲያ ተናግሮኛል››፣ ይህን ወሳኝ ትንቢት ከዚህ ቀን በኋላ ጀምረው እንዲሰሙት›› በሚል የሚለቀቁት ሐሰተኛ የትንቢት ቪዲዮዎች እና ጽሑፎች ብዙ ተከታዮችን በማግኘታቸው የግለሰቦችን ኪስ እያደለቡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ምእመናንን ከእምነት

እያናወጡ፣ በነገ ተስፋ እንዳይኖሩ እያደርጉ ነው።‹‹ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ታላላቅ ምልክትና ተአምራትን ያሳያሉ›› (ማቴ.፳፬፥፳፬) እንዳለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እምነቱን በደንብ ያውቃሉ የተባሉት ሁሉ የዚህ ሰለባ ሆነው ይታያሉና በጊዜ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል።

አንዳንዶች በቤተ ክርስቲያን ስም ተጠልለው የእግዚአብሔርን ሳይሆን የራሳቸውን ጉዳይ (ሐሳብ) ሲያራምዱ፤ በእግዚአብሔርም ስም የሐሰት ትምህርትን ሲያስተምሩ የሐሰት ትምህርትንና ትንቢትንም ሲናገሩ ዳር ቆመው የሚያዩ፣ ጉዳዩን እያራገቡ ከሰማው አካል ላልሰማው ሲያስተላልፉ የሚውሉ አካላት ከዚህ ኢ ክርስቲያናዊ ድርጊት እንዲቆጠቡ ቤተ ክርስቲያን አጥብቃ መልእክትን ልታስተላልፍ ይገባታል። በቤተ ክርስቲያን እና በመንፈሳውያን ስም የተከፈቱ ማኅበራዊ ሚዲያዎችም ቢሆኑ ነገ ለሚጠፋ፣ በምድር ላይ ለሚቀር ሀብትና ዝና ከመሥራት ይልቅ ለሰማያዊው መንግሥት የሚያበቃ እውነተኛ ወንጌልን በማስተላለፍ በየዋህነት የሚሄደውን ሕዝብ ሊታደጉት ይገባል።

በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ ማንነት በሚያጠለሽ መልኩ የሚካሄዱትን እንዲህ ዓይነት የሐሰት ትንቢቶች፣ ምእመኑን ከክርስትና ሕይወቱ እንዲፋታ የሚያደርጉ የቤተ ክርስቲያን ድምጽ ያልሆኑ ውዥንብሮች ባለመከተል እና ባለመስማት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ምእመናን የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል።የቤተ ክርስቲያን መምህራነ ወንጌልና አባቶች ስለ እንደዚህ ዓይነቶቹ ሐሰተኛ ነቢያት ትምህርት አደገኛነት በማጋለጥ፣ እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል በማስተማር ምእመኑን ሊታደጉት ይገባል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የራስዋ መዋቅራዊ አሠራር ያላት እንደመሆንዋ መጠን ዐውደ ምሕረቷን ከእንደዚህ ዓይነት እኩይ ተግባር በመከላከል ልታፀዳ ይገባታል። በራሳቸው መንገድ ሄደው በየመንገዱና በየማኅበራዊ ሚዲያው በቤተ ክርስቲያን ስም የሚነግዱትን ሐሳውያን ነቢያት በማውገዝና ምእመናን እንዳይከተሏቸው መልእክት በማስተላለፍ ወደጥፋት እየሄዱ ያሉትን መታደግ ዘመኑ ሚጠይቀው ትልቅ ሥራዋ ሊሆን ይገባል።

**እግዚአብሔር እንዲናገሩ ያዘዛቸውን የሚናገሩ፣ ሕዝቡን፣ ነገሥታቱን የሚገሥፁ፣ የሚመክሩ፣ የሚያስጠነቅቁ ፣ የሚያስተምሩ ቅዱሳን አባቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዛሬም እንዳሉ ይታመናል።ሆኖም ከዚህ በተቃራኒ የራሳቸውን ሥጋዊ ፍላጎት ለማርካት እና ተከታይ ምእመናንን ለማፍራት የሚባዝኑት ትንሽ አይደሉምና ጉዳዩ ቸል**

**የሚባል አይደለም።**

# ሐሰተኞች አጥማቂዎችና የቤተ ክርስቲያናችንንና የምእመናን ፈተናዎች

## •አጥማቂስ ማን? ስለጥምቀት ቤተ ክርስቲያን ምን ታስተምራለች? መጻሕፍትስ ምን ይላሉ?

ሻምበል ጥላሁን

**ክፍል ሁለት**

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦***

መቍጠሪያ በቤተ ክርስቲያናችን ለጸሎት መቀስቀሻና ማስታኮቻ የሚውል እንደሆነ የሚናገሩት ሙሐዘ ጥበባት ምእመናን እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ፣ በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ፣ ኪርያላይሶን የተባሉትን የምሕላ ጸሎቶች በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተመደበላቸውን ቍጥር ሳይስቱ እንዲጸልዩ የተሠራ ሥርዓት ነው በማለት ያብራራሉ። በጸሎት ጊዜ ዝንጋኤ እንዳይገጥማቸው ኅሊናቸውን ለመሰብሰብም ይረዳል የሚሉት ጸሐፊው አንድ ቅዱስ ለብዙ ዘመን የጸለየበት መቍጠሪያ፣የተደገፈበት መቋሚያ፣ የቆመበት ምድር፣ የለበሰው ልብስ፣ የተገለገለበት መጽሐፍ ተአምራት ቢያደርግ አይገርምም።

ቅዱሳን የነፍሳቸው ቅድስና ለሥጋቸው፣ የሥጋቸውም ለልብሳቸው፣ የልብሳቸው ለጥላቸው ተርፎ እንደሚፈውስ (በሐዋ. ፭፡፲፪-፲፯፤ ፲፱፡ ፲፩-፲፪) ተጽፎ እናነባለን ሲሉ የሚያስረዱት ጸሐፊው ከዚህ ውጭ ግን የሚሸጥ መቍጠሪያ ሰይጣን የሚያስወጣበት፣ ሰው ራሱን በመቍጠሪያ ስለደበደበ ከዲያብሎስ እሥራት የሚፈታበት ምንም ምክንያትና ሥርዓት የለም ይላሉ። ሰይጣን በጾምና በጸሎት እንጂ በመቍጠሪያ ድብደባ አይለቅም (ማቴ.፲፯፡፳፩)። ያ መቍጠሪያ ተአምር የሚሠራ ቢሆን እንኳን አንድ ቅዱስ የተጋደለበት፣ ከዚያ ቅዱስም በረከት ያተረፈ መሆን አለበት ልክ የቅዱስ ጳውሎስ የጨርቁ እራፊ ይፈውስ እንደነበረው ሲሉም ያስረዳሉ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክም የትኛውም አባት መቍጠሪያ ሲያድልና በመቍጠሪያ ሰይጣን ታወጣላችሁ ብሎ ሲያስተምር አልታየምም ይላሉ።

ጌታችን በሺዎች የሚቈጠር ሕዝብ አስተምሯል። በጌንሳሬጥ ምድር አምስት ሺ(ማቴ ፲፬፡፲፫-፳፩)፣ በገሊላ ባሕር አጠገብ አራት ሺ(ማቴ ፲፭፡፴፪-፴፱)፣ ይህ ሁሉ ሕዝብ የቃሉን ትምህርት የእጁን ተአምራት አይቶ ይኼድ ነበር እንጂ ሰይጣን አድሮበት በአንድ ጊዜ የጅምላ ጩኸት ሲጮህ ታይቶ አይታወቅም የሚሉት ሙሐዘ ጥበባት የተወሰኑ ሰዎች ግን እየቀረቡ ፈውሰ ሥጋ ፈውሰ ነፍስ ማግኘታቸውን ቅዱሱ መጽሐፍ ይነግረናል ይላሉ። በዚህ ጊዜም ቢሆን መድኃኒት ያደረገብሽ፣ ድግምት ያስደገመብህ፣መተት ያስመተተብህ እገሌ ነው የሚል ሰይጣን አልተሰማም። ዛሬ ግን በአንድ ቦታ ለጥምቀት የሚሰበሰቡ ሰዎች አብዛኞቹ ይጮኻሉ። ሁሉም በሰይጣን ተይዘዋል ይባላሉ፣ ሁሉም ድግምት፣ መተት፣ መድኃኒት፣ ጥንቆላ እንደተደረገባቸው ይነገራቸዋል። ሰይጣንን አምነው ከባሎቻቸው፣ ከሚስቶቻቸው፣ ከእኅት ወንድሞቻቸው፣ ከጎረቤቶቻች፣ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ይጣላሉ።

ከባቴ አበሳነትን ፈጽሞ የረሳ፣ ከፍቅር ይልቅ ጠላትነትን ለማስፈን የመጣ፣ ሰዎች እግዚአብሔርን አምነው ከመፋቀር ይልቅ ሰይጣንን አምነው እንዲጣሉ የሚያደርግ የሰይጣን አሠራር ነው። ለመሆኑ ይህንን ሁሉ ሕዝብ ሰይጣን ሲቈጣጠረው ኢየሱስ ክርስቶስ የለምን? የተጠመቅነው የልጅነት ጥምቀት፣ የቈረብነውስ ቍርባን አይሠራምን? ገና ወደ ክርስትና ያልመጡ የገሊላ ክርስቲያኖች እንኳን በጩኸት አልተደበላለቍም እንኳን እኛ በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉድ የተባልነው ብለው ይጠይቃሉ ጸሐፊው። ይህ አሠራር የክርስቶስን ነገረ ድኅነት የሚፃረርና ከማዳን ሥራውም የወጣ ነው በማለትም ይሞግታሉ። ከክርስቶስ ክብርና ኃይል ይልቅ የሰይጣንን ኃይል ለማሳየት የሚሠራም ነው ብለው ያምናሉ ሙሐዘ ጥበባት ዳንኤል።

ለመሆኑ ስመ እግዚአብሔርን የሚጠራ ሁሉ ትክክለኛ ነውን? የሚሉት ጸሐፊው፤ አንዳንድ ምእመናን እንዲህ ይላሉ ‹እግዚአብሔርን ይጠራሉ፣ እመቤታችንንም ያከብራሉ››። ልክ ነው ሰይጣን ለአመሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል። ሰይጣን ምንም እንኳ የሐሰት አባቷ ቢሆንም (ዮሐ. ፰፡፵፬) ሙሉ ውሸት ግን አይናገርም። በከፊል እንጂ። ሔዋንን ‹ንግሥተ ሰማይ ወምድር› ሲላት ከፍሎ ነው የዋሻት። ንግሥተ ምድር ናት፤ ንግሥተ ሰማይ ግን አልነበረቿም። በወንጌል ውስጥ አጋንንት ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው ያውቃሉ። ሰይጣን ጌታን ሲፈትነው ከቅዱሳት መጻሕፍት ጠቅሶ ነው(ማቴ. ፬)፤ ጌታችን በጌርጌሴኖን ያገኛቸው አጋንንት ያደሩባቸው ሰዎች ‹የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ› ብለው ነበር የተናገሩት። ንግግራቸው ልክ ነው። እነርሱ ግን አጋንንት

ናቸው፡፡ ጌታም አስወጣቸው እንጂ ማን ድግምት እንዳደረገባቸው አላናዘዛቸውም፡፡ በሌላ ቦታም በምኲራብ ሲያስተምር አንድ ሰይጣን ያደረበትን ሰው አመጡለት፡፡ ሰይጣኑም ‹‹የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ‹ ብሎ ነበር የጠራው፡፡ ጌታ ግን ‹ዝም ብለህ ወጣ› አለው እንጂ መድኃኒት ማን እንዳደረገ ተናገር አላለውም (ማር. ፩፣፳፩-፳፰)፡፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ ስላለውም ሰይጣንነቱን አልቀየረውም፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስተምር ፊልጵስዩስ የተባለ ከተማ ደረሰ፡፡ በዚያም አንዲት በርኩስ መንፈስ የተያዘች ሴት እየተከተለቺው ‹‹የመዳንን መንገድ የሚነግሯችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው›› አለች፡፡ ሴትዮዋ የተናገረቺው ምንም ስሕተት የለውም፡፡ እነ ቅዱስ ጳውሎስ የመዳንን መንገድ ያስተምራሉ፡፡ የልዑል አምላክ ባሪያዎችም ናቸው፡፡ ይህ ትክክል ስለሆነ ግን ቅዱስ ጳውሎስ ዝም አላለም፡፡ መንፈሱን አስወጣው እንጂ(የሐዋ.፲፮፣፲፮-፲፰)፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚነግሩን አንድ ሰው ስመ እግዚአብሔርን ወይም ስመ ቅዱሳንን ስለጠራ ብቻ ትክክል መሆኑን እንደማያሳይ ነው፡፡ እርስ በርሱ የማይጣረስ ርቱዕ የሆነ እምነትም ያስፈልገዋል፡፡ ርቱዕ የሆነ ሕይወትም ያሻዋል፡፡ በክርስትና አንድ ሰው መንገዱ ትክክል ሳይሆን ውጤቱ ትክክል ሊሆን አይችልም ይላሉ ጸሐፊው፡፡ ያለ ትክክለኛ እምነት፣ ያለ ትክክለኛም መንፈሳዊ ሕይወት ትክክለኛ ተአምራት ሊኖረው አይችልም የሚሉት ሙሐዘ ጥበባት በሲኦል በኩል ወደ ገነት ሊገባ አይችልም ይላሉ፡፡

**ጌታችን በሺዎች የሚቈጠር ሕዝብ አስተምሯል። በጌንሳሬጥ ምድር አምስት ሺ(ማቴ ፲፬፣፲፫-፳፩)፣ በገሊላ ባሕር አጠገብ አራት ሺ(ማቴ ፲፭፣፴፪-፴፱)፣ ይህ ሁሉ ሕዝብ የቃሉን ትምህርት የእጁን ተአምራት አይቶ ይኼድ ነበር እንጂ ሰይጣን አድሮበት በአንድ ጊዜ የጅምላ ጩኸት ሲጮህ ታይቶ አይታወቅም የሚሉት ሙሐዘ ጥበባት የተወሰኑ ሰዎች ግን እየቀረቡ ፈውሰ ሥጋ ፈውሰ ነፍስ ማግኘታቸውን ቅዱሱ መጽሐፍ ይነግረናል ይላሉ።**

ተአምራት ማድረግ ብቻውን የቅድስና ማሳያ አይደለም የሚሉት ጸሐፊው፡፡ ተአምራት ከመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት ሲመነጩ እንጂ፡፡ ተአምር ከመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት የመጣ ሲሆን ‹ስም በመንግሥተ ሰማያት በመጻፉ እንጂ በድንቅ ነገር ማንም ደስ አይለውም››(ሉቃ. ፲፣ ፲፯-፳)፡፡ ይላሉ ሙሐዘ ጥበባት፡፡ ተአምራትን ሲከተሉ መኖርም የአሕዛብነት ምልክት እንጂ የክርስትና ምልክት አይደለም የሚሉት ጸሐፊው፤(ማቴ. ፲፪፣ ፴፱)፡፡ የክርስትና ዋና መሠረቱ ክርስቲያናዊ ትምህርት፣ ክርስቲያናዊ እምነትና ክርስቲያናዊ ሕይወት ናቸው ይላሉ፡፡ አንዳንዶች በማርቆስ ወንጌል መጨረሻ ላይ(ማር ፲፮) ‹‹ያመኑት እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል›› የሚለውን ይጠቅሳሉ፡፡ እዚህ ላይ ያመኑት የተባሉት ‹የበቁት› ማለት ነው፡፡ ያማ ባይሆን ኖሮ ሁላችንም ተአምር ስናደርግ መኖራችን ነበር፡፡ አምነናልና፡፡ ደግሞም ያመኑት የሚለው ለሁላችንም ይሠራል ካልን እስኪ መርዝ ጠጥተን ምንም ሳንሆን፤ እባብም ጨብጠን ስንተርፍ እንየው ይላሉ ጸሐፊው፡፡

ይህ ሁሉ ግን በእምነት ለበሰሉ የሚቻል ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራም በሐዋርያት እጅ ያመኑት ሁሉ ተአምር ሲሠሩ አናይም፡፡ በሐዋርያት ሥራ ድንቅ ሲሠሩ የምናያቸው ክርስቲያኖችም በጸሎት የተጉ፣ በሐዋርያነት አገልግሎት ሰማዕትነት የከፈሉ፣ በገድል የተቀጠቀጡ ናቸው ይላሉ ጸሐፊው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ ሕይወቱ በተአምራት ከመገለጡ በፊት በሱባኤ የተወሰነ ነበረ (የሐዋ. ፲፫፣ ፩-፫) የዛሬ አጥማቂዎች ግን ማጥመቅ ፕሮፌሽናቸው እንጂ የመንፈሳዊ ሕይወታቸው መገለጫ አይደለም በማለትም ያስረዳሉ፡፡ እንዲህ ባለው ገዳም በገድል የኖሩ፣ እንዲህ ያለ መሥዋዕትነት ለክርስትና የከፈሉ ወይም ለምእመናን አርአያ የሚሆን እንዲህ ያለ መንፈሳዊ ሕይወት የነበራቸው ናቸው ተብሎ የማይመሰከርላቸው ራሳቸውን በራሳቸው የሾሙ ናቸው፡፡

የሰይጣን ምትሐትም አለ የሚሉት ጸሐፊው የሙሴ ጸጋና ሕይወት ድል እንዲሆኑ ባያደርጋቸው ኖሮ የፈርዖን ጠንቋዮች ብዙ አስደናቂ ነገር ሠርተው ነበር (ዘጸ.፯፣፰-፲፫)፡፡ በዘመነ ሳዖል የነበረቺው ሟርተኛም የሙታንን መንፈሶች ትጠራ ነበር (፩ኛ ነገሥት. ፳፰፣ ፰-፳፬)፡፡ አይሁድም አጋንንትን ያወጡ ነበር (የሐዋ. ፲፱፣፲፫)፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም የሐሳዊ መሲሕን አመጣጥ ሲያስተምረን ‹‹የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች፣ በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመጽም ማታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው›› ይላል የሚሉት ሙሐዘ ጥበባት (፪ኛ ተሰ. ፪፣፱)፡፡ ይህም ከመንፈሳዊ ብቃት የማይመጣ ተአምር፣ ድንቅና ምልክት ምንጩ ከሰይጣን

እንደሆነ ይጠቁመናል ይላሉ:: ዛሬ በእነዚህ ይህንን ያህል የምንታለል ከሆነ ነገ ሐሳዊ መሲሕ ከዚህ የሚበልጡ አስደናቂ ተአምራትን ሲያደርግ ጭልጥ ብለን መከተላችን የማይቀር ነው:: ‹‹የተመረጡትን እንኳን እስኪያስት ድረስ›› ተብሏልና:: (ማቴ.፳፬፥፳፬)

ምሥጢረ ቀንዲል መሠረቱን መጽሐፍ ቅዱስ ያደረገ (ያዕቆብ. ፭፣፲፫) ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ነው::የሚፈጸመው በካህናት ሲሆን የራሱ የሆነ የጸሎትና የመቀባት ሥርዓት አለው:: ለዚህም መጽሐፈ ምሥጢረ ቀንዲልን ማንበብ ይጠቅማል:: አሁን የምናየው ግን በጀሪካል ቅባት ይዞ ማከፋፈል፣ ምእመናን ከአጥማቂዎች ‹ቅብዐ ቅዱስ› ወስደው እንዲጠጡና እንዲቀቡ ማድረግ፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያልነበረ፣ በምሥጢረ ቀንዲል ያልተፈቀደና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የሌለ ነው በማለት ጸሐፊው ያስረዳሉ:: አንዳንድ አጥማቂዎችም ‹‹ከኢየሩሳሌም የመጣ ነው›› ይላሉ:: ከኢየሩሳሌም የሚመጣ የተለየ ቅባት የለም:: አንድን ቅባት ቅዱስ የሚያደርገው ጸሎቱና ሥርዓቱ እንጂ የተሠራበት ከተማ አይደለም የሚሉት ጸሐፊው ኢየሩሳሌም ውስጥ ግሪክ ኦርቶዶክሶች፣ ካቶሊኮች፣ የይሖዋ ምስክሮች፣ ፕሮቴስታንቶች፣ ሌሎችም አሉ::ከኢየሩሳሌም የመጣ ማለት ከየት የመጣ ነው? ምእመናን ለኢየሩሳሌም በጎ ኅሊና ስላላቸው ‹‹ከኢየሩሳሌም ተባርኮ የመጣ ›› ይባላል::ማን ባረከው? ብሎ የሚጠይቅ ግን የለም ይላሉ ሙሐዘ ጥበባት::

ከአክባሪው ይልቅ ከባሪው፣ ከሰጭው ይልቅ ተቀባዩ፣ ከጌታው ይልቅ አገልጋዩ የሚከብርበት ሥራ የእግዚአብሔር አይደለም የሚሉት ጸሐፊው መንፈሳዊ አገልግሎት ዓላማው እግዚአብሔርን ማክበር፣ አሕዛብም እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ማድረግ፣ ከመንገድ ጠራጊውም ይልቅ መንገዱን እንዲያገኙት ማስቻል ነው ይላሉ:: አሁን የምናያቸው "አጥማቂዎች" እና "ተአምራት" አድራጊዎች ግን ራሳቸውን የሚያከብሩ፣ ለእግዚአብሔር ክብር የማይሰጡ ሕዝቡ ቅዳሴና ትምህርት እየተወ እነርሱን በየሜዳው እንዲከተል የሚደርጉ፣ ሕዝቡ ንስሐ ከመግባት፣ ሥጋወ ደሙ ከመቀበል ይልቅ የእነርሱ አድናቂና ካዳሚ እንዲሆን የሚሰቡ ናቸው ይላሉ:: ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ስለ ራሱ ሲናገር "እኔ ዝቅ ዝቅ ልል፣ እርሱም ከፍ ከፍ ሊል ይገባል" ነበር ያለው በማለት ያስረዳሉ፤ (ዮሐ. ፫፣፳፱):: ለእነ ቅዱስ ጳውሎስም በልስጥራ እግሩ የሰለለውን ሰው በፈወሰው ጊዜ ሕዝቡ ተደንቆ እንደ አምላክ ሊሠዉላቸው ወድደው ነበር:: ቅዱስ ጳውሎስ ግን "እንደ እናንተ ሰዎች ነን" እያለ ለምኖ አስተዋቸው:: (የሐዋ.፲፬፣፰-፲፰) ሕዝቡንም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መለሳቸው፤ የእግዚአብሔርም ስም እንዲከብር አደረገ ይላሉ::

በእነዚህና በሎችም ምክንያቶች በዘመናችን የተነሡትን ‹አጥማቂ ነን› ብለው ማስታወቂያ የሚያስነግሩትን፣ መቍጠሪያና ቅብዐ ቅዱስ የሚያከፋፍሉትን፣ በየሜዳው ሕዝብ ሰብስበው ምትሐት የሚሠሩትን ሰዎች መቀበል የለብንም:: ቤተ ክርስቲያን የጸጋው ግምጃ ቤት ናት:: በጸሎት የሚተጉ፣ በእምነት ሕይወት ያሉ ክርስቲያኖች በየምሕረት አደባባዮች ምሕረትን ያገኛሉ::በቤተ ሳይዳ መልአኩ ውኃውን ይባርከው እንደነበር ሁሉ የጠበል ቦታዎችን ራሱ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ባርኳቸዋል::

የክህነት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው እንጂየተለየ አጥማቂ አያስፈልጋቸውም:: ደግሞም ሁሉም ሕመም መዳን የለበትም:: ደዌ ዘእሴት (ለበጎ የሚሰጥ ሕመም) አለ:: ቅዱስ ጳውሎስ በብዙዎች ያደረውን ሰይጣን እያስወጣ እርሱን ግን የሚጎስመው ሕመም ነበረው:: ጌታን ሲለምንም ‹‹ተወው›› ነው የተባለው (፪ኛቆሮ. ፲፪፣ ፯):: የዛሬ አጥማቂ ነን ባዮች ግን ሁሉም ሕመም ይድናል ይላሉ:: ለቅዱስ ጳውሎስ ያልተቻለ ተቻላቸውን? ከሐዋርያት አንዱ የነገረው ያዕቆብ እግረ በሽተኛ ነበር (ዜና ሐዋርያት፣ በእንተ ያዕቆብ ሐዋርያ)፤ እርሱ ግን ብዙዎችን ይፈውስ ነበር:: ከእግዚአብሔር ምሕረት አገኘን የምንለውም ስንፈወስ ብቻ መሆን የለበትም፤ የምንታገሥበት ዐቅም ስናገኝም ጭምር እንጂ::

ልመናችንም ለፈውስ ብቻ ሳይሆን ለመታገሥ ዐቅም እንዲሰጠን መሆንም አለበት:: እግዚአብሔር ሁሉን ለመፈውስ የሚችል ቢሆንም ሁሉንም ግን አይፈውስም:: ለበረከት፣ ለተግሣጽ፣ ከከንቱ ውዳሴና ከትዕቢት ለመከላከል የሚፈቅደው ደዌም አለ:: ያዕቆብ ወልደ ይስሐቅ ይህ ተሰጥቶት ነበር (ዘፍ. ፴፪፣፴፭):: ክርስትና በመንፈሳዊ ሕይወት በመኖር፣ በንስሐ መንገድ መመላለስ፣ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በመሳተፍ እንጂ በድንቅና በተአምራት የሚኖር አይደለም:: አጋንትም ስለ ተናገረ እውነት ተደርጎ አይቈጠርም፤ ጋኔን የሀሰት አባት ተባለ እንጂ::

ይቆየን

# በዐረፍተ ዘመን የተገቱ የአባቶቻችንን ተጋድሎ እናስቀጥል

ካሳሁን ለምለሙ

**ክፍል አንድ**

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ምሁራንና ሊቃውንት መገኛ ሀገር ናት። ሊቃውንትን በማፍራት ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማይተካ ሚና ተጫውታለች። ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ትውልዱ በሥነ ምግባር ታንፆ እንዲያድግ፣ በዕውቀት የዳበረ አዕምሮ እንዲኖረው፣ ሀገር በቀል ዕውቀት እንዲስፋ፣ በአንጻሩም መሃይምነት እንዲጠፋ፣ ሀገር በሀገር በቀል ዕወቀት ምርምር ተጠቃሚ እንድትሆንና ሀገር በዓለም ዘንድ በአወንታ እንድትታወቅ እንዲሁም በራሱ የሚተማመን፣ አንገቱን የማይደፋና በሀገሩ የማያፍር ብርቱ ትወልድ እንዲፈጠር ከፍተኛ ጥረት አድረገዋል፤ እያደረጉም ይገኛሉ።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ከቤተ መቅደስ አገልግሎት በተጨማሪ የዕውቀት ማኅደር ሆነው ያገለግላሉ፤ ያስታራቂነትና የሽምጋይነት ድርሻም ይወስዳሉ። አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ብራና ፍቀው፣ ቀለም በጥብጠው፣ ብዕር ቀርፀው ቅዱሳት መጻሕፍትን ጽፈዋል። ይጽፋሉም። በዋናነት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ያለ ተተኪ አገልጋይ እንዳትቀር አገልግሎቷ እንዳይታጠፍ በርትተው ያስተምራሉ፤ የዘረጉት ወንበር እንዳይታጠፍ ይተጋሉ፤ ወንበራቸውን የሚተካ የአብነት መምህራንን ያወጣሉ። እነዚህ አባቶች ዐረፍተ ዘመን እስኪገታቸው ያገለግላሉ፤ ይወጣሉ፤ ይወረዳሉ።

በርካታ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲንን በማፍራት የማይታማው የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ዛሬም እንደተላንቱ አራት ዐይና ሊቃውንትን አፍርቶ ለቤተ ክርስቲያን ማበርከቱን አላቋረጠም። ከልጅነት እስከ ዕውቀት ቤተ ክርስቲያንን በበርካታ ዘርፎች የሚያገለግሉና እያገለገሉ ያሉ ሊቃውንት አባቶች እንዳሉ ሁሉ፤ የአገልግሎት ዘመናቸው በዐረፍተ ዘመን የተገታ በርካቶች ናቸው።

የዚህ እትም የቤተ አብርሃም እንግዳችን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከበጌምድር አውራጃ የተገኙት መልአከ መንክራት መንግሥቱ በላይ ሲሆኑ፤ እኝህ አባት ዐረፍተ ዘመን እስከገታቸው ጊዜ ድረስ ቤተ ክርስቲያንን ያለ ዕረፍት በቅንነት አገልግለዋል። ፈጣሪ የሚወደውን፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅመውን፣ ትውልድ የሚያንጸውን፣ የሰውን ልጅ ከመጥፎ ተግባር የሚመልሰውን እንዲሁም ከልጅነት እስከ ዕወቀት ከአባት የሚጠበቀውን ሁሉ አበርክተው በሕይወተ ሥጋ ተለይተዋል።ዝግጅት ክፍላችንም የአባታችንን የሕይወትና የአገልግሎት ጉዞ በአጭሩ ቃኝቶታል።መልካም ንባብ።



መልአከ መንክራት መንግሥቱ

መልአከ መንክራት መንግሥቱ በላይ ከአባታቸው ከብላታ በላይ ተሾመና ከእናታቸው ከወ/ሮ ሙሉ ኃይሉ ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፯ዓ.ም በጎንደር ክፍለ ሀገር ወረታ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ስሙ ወፍ አምሳ በተባለው ቦታ ተወለዱ። የልጅነት ጊዜያቸውን ያሳለፉበት በተወለዱበት የገጠር መንደር ሲሆን ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም ከታላቁ የቅኔ መምህር ወልደ ሚካኤል ዘንድ መሠረታዊ የሚባሉ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶችን ተምረዋል። ፊደልና ንባብ እንዲሁም መዝሙረ ዳዊትን ተከታትለዋል።

ከዚያም ከኒህ ታላቅ መምህር ቅኔን ከነአገባቡ እንዲሁም ከነ እርባ ቅምሩ በታላቅ ትጋት ተምረዋል፡፡ ሲያስተምሯቸው የቆዩት መምህር ሲሞቱባቸው በ፲፬ ዓመታቸው ከሌሎች የዕድሜ እኩያ ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን በራሳቸው ፍላጎት ወደ ጉራ አባ ደብረ ገነት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ከታላቁ የድጓ መምህርና የደብሩ አስተዳዳሪ ከሆኑት መልአከ ምሕረት መምህር ፈጠነ አዲሱ ዘንድ የዳዊትና የዜማ ትምህርታቸውን በመቀጠል ምዕራፍ፣ ና ጾመ ድጓና ድጓ የተባሉትን ያሬዳዊ ጸዋትወ ዜማዎች በሚገባ አጠናቀዋል፡፡ በወቅቱ መልአከ መንክራት መንግሥቱ በላይ ጎበዝ የድጓ ተማሪ መሆናቸውን የተመለከቱት መምህራቸው ንብረትነቱ የደብሩ የሆነውን ትልቅ የብራና ድጓ መጽሐፍ ሰጥተው ሲያስተምሯቸው ከቆዩ በኋላ አርቆ አሳቢው ሊቅ መልአከ መንክራት መንግሥቱ ግን የደብሩ ድጓ የሀገርና የሕዝብ ንብረት መሆኑን በመረዳት ለራሳቸው የሚሆን የድጓ መጻሕፍ አዘጋጅተው ትምህርታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ይህ በእርሳቸው እጅ የተጻፈው የድጓ መጽሐፍ በአሁኑ ሰዓት በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት በፎገራ ወረዳ ለምትገኘው ሻጋ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በስጦታ መልክ ተበርክቶ በአገልግሎት ላይ ይገኛል፡፡

መልአከ መንክራት መንግሥቱ ይህንን የድጓ መጽሐፍ ለመጻፍ ፲ ዓመታት እንደፈጀባቸውም ይነገራል፡፡ መጽሐፉን ጽፈው ከጨረሱም በኋላ በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት የድጓ ማስመስከሪያ ወደሆነችው ቅድስት ቤቴልሔም በመሄድ ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር ቆይታቸው የጻፉትን ድጓ አርመው ይትበሀል፤ ወጉንና አመሉን በመጠንቀቅ ድጓውን አስመስክረዋል፡፡ ድጓውን ያስመሰከሩት ፲፱፻፶ ዓ.ም ሲሆን በወቅቱ ዕድሚያቸው ፳፬ እንደነበረ የግል ማኅደራቸው ያመለክታል፡፡ ድጓውን አስመስክረው ከተመለሱ በኋላ ከቀለም አቀባበላቸውና ከጽሑፍ አጣጣላቸው የተነሳ በታላቁ የድጓ መምህር መምህር አምሳሉ አማካይነት "መልአከ መንክራት" ተብለው ስመ ክብር ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚያን ጊዜም ጀምሮ በዚህ የማዓርግ ስም መልአከ መንክራት መንግሥቱ በላይ ተብለው ሲጠሩ ኖረዋል፡፡

ድጓውን አስመስክረው ከቤተልሔም ከተመለሱ በኋላ በተወለዱበት ቦታ ወረታ ደብረ መንክራት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ አስፍተው፣ ወንበር ዘርግተው ደቀ መዛሙርትን እያስተማሩ በነበሩበት ወቅት በደረሰባቸው የጤና እክል ምክንያት ተዘዋውረው ፀበል ተጠምቀው ጤናቸው ተመልሶላቸው ቤተ ክርስቲያንን በሙያቸው ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ መልአከ መንክራት መንግሥቱ ደብረ መንክራት ወረታ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በዕድሜ ብዛት ፈርሶ በነበረበት ወቅት ከ፲፱፻፷፪ - ፲፱፻፷፬ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ፕላን እንዲሠራ ጥረት በተደረገበት ጊዜ የሥራው ዋና አስተባባሪና ገንዘብ ያዥ በመሆን እንዲሁም የራሳቸውን ሃያ አምስት ሺህ ብር በመለገስ ለቤተ ክርስቲያኑ እድሳት ታላቅ አስተዋጽ አድርገዋል፡፡በዚህም ለቤተ ክርስቲያኑ እድሳት ባበረከቱት አስተዋጽኦም የምስጋና ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል፡፡

በወቅቱ በሠሩት መንፈሳዊ ሥራ አማካይነት ጠቅላይ ቤተ ክህነት ድረስ ተጠርተው ወደ ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተልከው በድጓና ቅኔ ትምህርቶች የሰባት ወር ሥልጠና ወስደው በሰርተፍኬት ተመርቀዋል፡፡ ከዚያም በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ጀምሮ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓተ መንግሥት ወድቆ በደርግ ሥርዓተ መንግሥት ሲተካ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይፈለጉ ስለነበር በሕዝብ ተመርጠው ከቀበሌ እስከ ሀገር አቀፍ ድረስ ሕዝብን በታማኝነትና በቅንነት ሲያገለግሉና ሲመሩ ቆይተው የደርግ ሥርዓተ መንግሥት ኢሰፓኮን ሲመሠርት ሥርዓቱን ባለመቀበላቸው ሕዝብ እየወደዳቸው በራሳቸው ፈቃድ ሥልጣናቸውን ለቀው ወደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተመልሰዋል፡፡

የደርግ ሥርዓተ መንግሥት ወድቆ የኢሕዴግ ሥርዓተ መንግሥት ሲመሠረት መልአከ መንክራት መንግሥቱ በወረታ ከተማ ማኅበራዊ ፍርድ ቤት የፍርድ ሸንጎ በመሆን ተሹመው ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ጠቢቡ ሰለሞን ‹‹ጊዜ ለኵሉ›› ብሎ እንደተናገረው ቀደም ብለው ባቀረቡት የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ጥያቄ መሠረት በብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ መልካም ፈቃድ ካላቸው የድጓና የቅኔ መምህርነት ሙያ በተጨማሪ የፎገራ ወረዳ ቤተ ክህነት ዋና ጸሐፊና ገንዘብ ያዥ ሆነው ተመድበዋል፡፡ በወቅቱ አገልግሎታቸውን ይፈጽሙ የነበረው ያለምንም ወርኃዊ ደምወዝ ነበር፡፡በአሁኑ ሰዓት የወረታ ወረዳ ቤተ

ክህነትና የፎገራ ወረዳ ቤተ ክህነት የሚገለገሉበት ባለ አምስት ክፍል ቢሮና አንድ ትልቅ አዳራሽ አሠርተዋል፡፡ ለዚህ ሥራቸውም የደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ እጅ የዕውቅናና የማበረታቻ የምስክር ወረቀት ተሸልመዋል፡፡ የወረዳ ቤተ ክህነት አገልጋይ ሆነው እያሉ የወረታ ደብረ መንክራት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን በዋና አስተዳዳሪነትን ደርበው እንዲሠሩ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያንን በሰላምና በፍቅር ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ እያገለገሉ ሳለ ከተማው እየሰፋና ቤተ ክርስቲያን የምታስተምራቸው ምእመናን እየበዙ በመምጣታቸው የሕዝበ ክርስቲያኑ ፍላጎት ተጨምሮበት በብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ መልካም ፈቃድ የወረታ ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን አስተክለዋል፡፡

የተተከለውን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ደረጃውን በማሻሻል በአጭር ጊዜ ውስጥ ውብ እና ግዙፍ የሆነ ሕንፃ አድርገው በማጠናቀቅ ቅዳሴ ቤቱን አክብረዋል፡፡ ሁለት አብያተ ክርስቲያናትን በአንድ ላይ በማስተዳደር መልካም የሕዝብ እረኝነታቸውንም አስመስክረዋል፡፡ መልአከ መንክራት መንግሥቱ ሩቅ አሳቢና ጥንቁቅ ምሁር የነበሩ ሲሆኑ ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸውን ችለው በራሳቸው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቢመሩ ለአገልግሎት አመቺ ይሆናል በማለት በራሳቸው ፈቃድ ለሁለቱ አድባራት ማለትም ለወረታ ማየ ቀራንዮ ደብረ ገነት መድኃኔዓ ለምና ለደብረ ብሥራት ወረታ ቅዱስ ገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎችን በማስመደብ አገልግሎታቸው እንዲሰፋና በተለያየ መንገድ ራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ ሐዋርያዊ ተልኮአቸውን ተወጥተዋል፡፡ የወረታ ደብረ መንክራት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ለአካባቢው ምእመናን ሩቅ በመሆኑ በአቅራቢያ በሚገኘው ልዩ ስሙ ጉብና በተባለው ጎጥ ቤተ ክርስቲያን በማሠራት በብፁዕ አቡነ ሚካኤል አባታዊ ቡራኬ ታቦተ ቅዱስ ሚካኤልን አስገብተዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያኑ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ተብሎ እንዲሰየምም የግል ጥረት አድርገዋል፡፡ ይህንንም ቤተ ክርስቲያን ከወረታ ደብረ መንክራት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ላይ አድርገው ሲመሩ ከቆዩ በኋላ በዚሁ ታላቅ ደብር ሲያገለግሉ የነበሩ ካህናትን ለአዲስ ደብር በመመደብ ራሱን ችሎ በሰበካ ጉባኤ እንዲመራ አድርገዋል፡፡ በአገልግሎት ላይ በነበሩበት ወቅት ወላጆቻቸው ሚስት አግብተው ትዳር መሥርተው እንዲኖሩ በመፈለጋቸው በወቅቱ ወይዘሮ እማኜ ኃይሉ ከተባለች ወጣት ጋር ጋብቻ ፈጽመዋል፡፡ ከቤተሰቦቻቸው ዘንድ ሰፊ የእርሻ መሬትና ብዙ የቀንድ ከብት ተሰጥቷቸው በረዳት ገበሬዎቻቸው በማሳረስ ከፍተኛ የሆነ ምርት በማግኘትና የእንስሳት ርባታ በማካሄድ ትዳራቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በደስታና በፍቅር ይመሩ ነበረ፡፡ መልአከ መንክራት መንግሥቱ በላይ የተቸገረን የሚረዱ፣ ሰዎችን የሚመክሩ፣ ደግ ሩኅሩኅ፣ አስታራቂና የሰላም አባት ነበሩ፡፡ መልአከ መንክራት መንግሥቱ የስምንት ሴቶችና የአምስት ወንድ ልጆች አባት ሲሆኑ ልጆቻቸውን በሥርዓት በማሳደግና ትምህርት አስተምረው ለቁም ነገር በማብቃት ልጆቹም በመንግሥት ሥራ ተሰማርተው የራሳቸውን ሕይወት ከመምራት ባሻገር ቤተ ክርስቲያንን በተለያየ መንገድ እያገዙ ይገኛሉ፡፡ አንዳንድ ልጆቻቸውም ባለጸጋ በመሆናቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ይደግፋሉ፤ ያለ ደምወዝም አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ አባታቸውም እንደዚሁ በቤተ ክርስቲያን ያለ ደመወዝ ለረጅም ዓመታት ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡

መልአከ መንክራት መንግሥቱ ዐረፍተ ዘመን እስከገታቸው ድረስ በታላቁ ደብር በወረታ ደብረ መንክራት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ቴራዞ እንዲነጠፍ በማድረግ ረገድ ታላቁ የልማት አርበኛ አባት ነበሩ፡፡ በድጓና በቅኔ ሙያ እያገለገሉና ቤተ ክርስቲያንን እያስተዳደሩ ከቆዩ በኋላ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት አዲስ አበባና ባሕር ዳር በግልና በመንግሥት የጤና ተቋማት ሲረዱ ቆይተው በተወለዱ በ፹፯ ዓመታቸው መስከረም ፳፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ዐርፈዋል፡፡ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ፣ የደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅና የሥራ ኃላፊዎች፣ የደብረ ታቦርና የአዲስ ዘመን ወረዳ ቤተ ክህነት ሠራተኞች፣ የየአካባቢው ሊቃውንት፣ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት ተወልደው ባደጉበት፣ ሲያገለግሉና ሲያስተዳድሩ በነበሩበት በታላቁ ደብር በወረታ ደብረ መንክራት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው ተፈጽሟል፡፡

# የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጠንቅቀው የተማሩ ወጣቶች የትውልድንና የሀገርን ስብራት ይጠግናሉ



ከግራ ወደ ቀኝ መምህር ጥበቡ ጌታቸውና አቶ ምትኬነህ ዓለማየሁ

ካሣሁን ለምለሙ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ወንጌልን ስትሰብክ ቆይታለች፤ እየሰበከችም ትገኛለች። ከዚህም ባሻገር የሀገር በቀል ዕውቀት ምንጭ ሆና እያገለገለች ትገኛለች። ቤተ ክርስቲያን ካሏት የትምህርት ዘርፎች መካከል ደግሞ የአብነት ትምርት፣ የነገረ መለኮት ትምህርት፣ የሰንበት ትምህርት በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ እነዚህ ትምህርቶች ሳይቋረጡ ለዘመናት ለትውልዱ ሲሠጡ ቆይተዋል። በተለይም ወጣቱ ትውልድ ከቤተ ክርስቲያን እንዳይርቅ በሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ትምህርቶች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ሰንበት ትምህርት ቤቶች በየአጥቢያው ከተቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ ትውልዱ ቤተ ክርስቲያንንና ሥርዓቷን ጠንቅቆ እንዲያውቅ ከማድረግ አኳያ የማይተካ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ። ይህ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ድርሻም በትውልዱ የፀባይ ለውጥ ያመጣ ሲሆን ይህም በሀገር ዕድገት ላይ የራሱ የሆነ አወንታዊ ለውጥ ይኖረዋል።

ሰንበት ትምህርት ቤቶችን ስናስብ ኦርቶዶክሳዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ ቃለ እግዚአብሔር ተምረው ባሕርየ እግዚአብሔርን ተረድተው እንዲያመልኩ፣ሕጉን ጠብቀው በሃይማኖት፣በምግባር እና በትሩፋት ፀንተው አምላካቸውን መስለው እንዲኖሩ የእርሱ የሆነችውን መንግሥተ እግዚአብሔርን እንዲወርሱ ታደርጋለች። ቤተ ክርስቲያን ዘላለማዊ የሆነውን የአምላክን ቃል ለተተኪው ትውልድ ከምታስተላልፍባቸው መንፈሳዊ ተቋማት አንዱ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ ጎልማሳዎች በኅብረት ሆነው የቤተ ክርስቲያንን ዶግማ፣ ቀኖና፣ ትውፊትን፣ሥርዓት እና መሰል ጉዳዮችን የሚማሩበት መንፈሳዊ ተቋሚ አንዱ ሰንበት ትምህርት ቤት ነው።

ያለ ሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት ሲወረድ ሲዋረድ የመጣውን ኦርቶዶክሳዊ እምነትና አስተምህሮ ማስቀጠል አይቻልም። ልጆቻችንም ኦርቶዶክሳዊት እምነትን፣ ዶግማን፣ ሥርዓት እና ትውፊትን በሰንበት ትምህርት ቤት ካልተማሩ ሃይማኖታቸውን ጠብቀው ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ አይቻላቸውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ልጆችን ወደ ቤተ እግዚአብሔር ልኮ ማስተማር እንደሚገባ ሥርዓቱም እንደነበር በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም ሰፍሮ

የሚገኝ ሲሆን ይህም በዘመናችን ላለችው ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት፣የወጣቶች እና የጎልማሶች ማስተማሪያ ለሆነችው ሰንበት ትምህርት ቤት መነሻ የሆነ እና መሠረትነቷም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ ማረጋገጫ ነው። ይሁን እንጂ ከዚህ ቀደም ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች የምትሰጠው ትምህርት ወጥ፣ተከታታይና በሥርዓተ ትምህርት ያልታገዘ ነበር። በሰንበት ትምህርት ቤቶች ይሰጥ የነበረው ትምህርት የተስፋፋና በዘልማድ የሚሰጥ በመሆኑም በትውልዱ ላይም እንደ ሀገር ተፈላጊው ለውጥ መጥቷ ተብሎ አይታሰብም። ይህንን ችግር ለማቃለልም ሆነ ከዚህ ቀደም የነበረውን የትምህርት አሰጣጥ ወጥ በሆነ ሥርዓተ ትምህርት ለመደገፍ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ እገዛ የአዲስ አበባ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት በሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ትምህርቶችን በሥርዓተ ትምህርት የተደገፈ ለማድረግ በቅርቡ ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾ በትግበራ ላይ ይገኛል። ዝግጅት ክፍላችንም በሀገር ዓቀፍ የሰንበት ትምህርት ቤቶች የትምህርትና ሥልጠና አስተባባሪ እንዲሁም በሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ ላይ ተሳተፎ ካደረጉት አቶ ምትኬነህ ዓለማየሁ እና በሀገር አቀፍ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ውስጥ የትምህርትና ሥልጠና ክፍል አስተባባሪ ከሆኑት መምህር ጥበቡ ጌታቸው ጋር አጭር ቆይታ አድረጓል። መልካም ንባብ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ከመቼ ጊዜ ጀምሮ እንደተደራጀና**

ሰንበት ትምህርት ቤቶች ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን እያበረከቱት ያለውን አስተዋፅኦ ቢገልጹልን?

**አቶ ምትኬነህ ዓለማየሁ፡-** የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት መደራጀት የጀመረው ከረጅም ዓመታት በፊት ቢሆንም በአዲስ መልኩ የተቋቋመው ደግሞ ከ፲፱፻፹፰ዓ.ም ጀምሮ ነው። በዚያ ዘመን የነበረው የሰንበት ትምህርት ቤቶች መዋቅርም የተለያየ ቅርፅ ስለነበራቸው በ፳፻፲፬ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ሥርዓት ይዘው፣ መመሪያ ተዘጋጅቶላቸው፣ በአንድ ወጥና በሀገር አቀፍ ደረጃ "የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት" በሚል ስያሜ ተቋቁሟል። በዚህ ወቅት የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት አዲስ አበባን ጨምሮ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ባሉ አህጉረ ስብከት ተግባራዊ ሆኖ በመልካም እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። እንደሚታወቀው በሀገራችን በሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚሳተፉት ወጣቶችና ሕፃናት ቊጥር እጅግ ከፍተኛ ነው።

ይህ መሆኑም ከሕፃናት እስከ ጎልማሳ ባለው የዕድሜ ክልል ያሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሃይማኖታቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ፣ በሥርዓት እንዲያድጉ፣ በመልካም ሥነ ምግባር እንዲቀረጹ አድርጓቸዋል። ሀገራቸውንና ቤተሰቦቻቸውን መውደድን፣ ቤተ ክርስቲያናቸውን በሁሉም ረገድ ማገዝንና ታላላቆቻቸውን ማክበርን ልጆች በሰንበት ትምህርት ቤት ቆይታቸው ከሚያገኟቸው ቁምነገሮች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። ልጆች በሰንበት ትምህርት ቤት ማለፋቸው ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ሀገር ብዙ አትርፈዋል። ሰንበት ትምህርት ቤቶች በዘመናችን በየአህጉረ ስብከቱ ባሉ አጥቢያዎች ሁሉ አሉ። እያንዳንዱ አጥቢያ ሰንበት ትምህርት ቤት የማዋቀር ኃላፊነት ስላለበት ሰንበት ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የሚበጁ ሕፃናትና ወጣቶችን በማፍራት ላይ ይገኛሉ።

እነዚያ በየአጥቢያው ያሉትን ሰንበት ትምህርት ቤቶች በአንድ መዋቅር በጋራ የሚመራቸው ደግሞ "የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት" ይባላል። የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት በሰንበት ትምህርት ቤቶች መካከል የጋራና ማእከላዊ የሆነ አሠራሮችን ይፈጥራል። አንድነቱ ሰንበት ትምህርት ቤቶች በወረዳም ሆነ በሀገረ ስብከት ደረጃ ወጥ የሆነ ሥራ እንዲሠሩ ያግዛቸዋል። ወጥ የሆነ ሥራ ለመሥራትና በሰንበት ትምህርት ቤቶች በኩል የሚሰጡ መንፈሳዊ ትምህርቶች በሥርዓተ ትምህርት መመራት ስላለባቸው በቅርቡ የሰንበት ትምህርት ቤት አንድነት ሥርዓተ ትምህርት ቀርጾ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። የተቀረጸው ሥርዓተ ትምህርት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ወጥና ተከታታይነት ባለው መልኩ ለማስተማር ያግዛቸዋል።

በየአጥቢያው ያሉ ሕፃናት፣ ወጣቶችና ጎልማሶች በሰንበት ትምህርት ቤቶች ሲሳተፉ የተለያዩ ትምህርቶችን ይማራሉ። ከዓለማዊ ትምህርታቸው ጎን ለጎን እንደየ ዕድሜያቸው የሚማሩበት በሰንበት ትምህርት ቤት አሠራር ተዘርግቶላቸዋል። ይህ አሠራር የተዋጣለትና ወጥ እንዲሆን ደግሞ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ያሉ ተማሪዎችን ያካተተ ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጿል። ሁሉን አቀፍ ሥርዓተ ትምህርት የታገዘው የሰንበት ትምህርት ቤት ትምህርት ልጆች በሀገራችን በመደበኛ (በዓለማዊ) ትምህርታቸው የተሻለ ተማሪዎች

እንዲሆኑም ያግዛቸዋል። በማኅበራዊ ኑሯቸውም የተሻሉ ከመሆናቸው ባሻገር ራሳቸውን ችለው ሌሎችን በሁሉም ዘርፍ እንዲደግፉ እገዛ ያደርግላቸዋል።

ይህም ከአጥቢያ እስከ ማእከል ድረስ ላሉ ወጣቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲኖረው የቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎትም ፈጣንና ዘመን ተሻጋሪ ለማድረግ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ትምህርት ወጥና ተከታታይ በሆነ ሥርዓተ ትምህርት መመራቱ ወሳኝ ሂደት ነው።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ሰንበት ትምህርት ቤት መቼ ተመሠረተ? ትምህርትስ እንዴት ያስተምሩ ነበር?**

**መምህር ጥበቡ ጌታቸው፡-** ሰንበት ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ከምታስፋፋበት መንገድ አንዱ ነው። ሰንበት ትምህርት ቤቶች በዋናነት የተቋቋሙት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘመን ሲሆን የቤተ ክርስቲያን ሂደታዊ ለውጥና ቃለ ዓዋዲ ሲጸድቅ አብረው እንደተቋቋሙ ይነገራል።ሰንበት ትምህርት ቤቶች ከመቋቋማቸው በፊት የተለያዩ የሰንበት ትምህርት ቤት ቅርጽ ያላቸው እንቅስቃሴዎች ነበሩ። በተደራጀና በተዋቀረ መንገድ ባይሆንም የሰንበት ዓይነት ትምህርት ሰንበት ትምህርት ቤቶች በይፋ ከመቋቋማቸው በፊት ነበረ። ወጣቶች ዘመናዊ ትምህርት ሲማሩ ጉድለት እንዳይኖርባቸው፣ ቤተ ክርስቲያናቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ሲባል ሁለቱን (መንፈሳዊና ዘመናዊውን ትምህርት) ለማጣጣም ሰንበት ትምህርት ቤት ተመሥርቷል።

ከዚህ ቀደም የነበሩት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጥ በሆነ ሥርዓተ ትምህርት አይመሩም ነበር። ነገር ግን በተከታታይ ትምህርትና በተምህሮ ማስተማር ዘዴ ትምህርቶች ከሕፃናት እስከ አዋቂ ድረስ ይሰጡ ነበር። ተከታታይ ትምህርቶችን ከሚያስተምሩ አጥቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሚገኘው የአራዳ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተጠቃሽ ነው። በአዲስ አበባ የሚገኙ አጥቢያዎች እርስ በእርሳቸው ልምድ እየተለዋወጡ ትምህርቶችን በኮርስ ደረጃ ያስተምሩ ነበር። እነዚህ ትምህርቶች በአብዛኛው በስብከት መልኩ የሚሰጡ ናቸው።ይሰጡ የነበሩት ትምህርቶች ይዘት (Course outline) እንጂ የቅርፅ፣ የደረጃና የሥርዓተ ትምህርት ደረጃ አላባውያንን የሚያሟሉ አልነበረም። በዚህ ሁኔታ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የራሳቸው የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ሊኖራቸው አልቻለም።

**ስምዐ ጽድቅ፡- አዲሱ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት የተቀረጸው ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው? በቀረጻው ወቅት ተሳትፎ ያደረጉ አካላትና በምንጭነት ጥቅም ላይ የዋሉት እነማን ናቸው?**

**መምህር ጥበቡ፡-** የሰንበት ትምህርት ቤቶችን ሥርዓተ ትምህርት ለመቅረፅ እንቅስቃሴ የተጀመረው የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ፅንሰ ሐሳብ በመነጨበት ወቅት ነው። የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በሰንበት ውስጥ ትምህርት ቤቶች አንድ ወጥ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ እንዲሆን የበኩሉን ድርሻ ያደረገ ሲሆን የሊቃውንት ጉባኤም የራሱ አስተዋጽኦ ነበረው።

በተለይ የሰንበት ትምህር ቤቶች መማሪያ መጻሕፍት ምን መሆን እንዳለባቸው ሊቃውንቱ በከፍተኛ ይደክሙ ነበረ። በመጽሐፍ ደረጃ የተዘጋጀው የሰንበት ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት በርካታ ምንጮችን ተጠቅሟል። ተቀርጾ በትግበራ ላይ ላለው ሥርዓተ ትምህርት ግብአት ከሆኑት ምንጮች መካከል ደግሞ የአብነት ትምህርት አንዱ ነው። የሰንበት ትምህርትን በተከታታይና ይሰጡ የነበሩ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ጭምር በግብአትነት ጠቀሜታ ላይ የዋሉ ሲሆን የአኀት አብያተ ክርስቲያናት የሥርዓተ ትምህርት፣ ልምድና ተሞክሮም በግብአትነት ተወስዷል። ለአብነትም የግብፅ፣ የአርመንና የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ልምድና ተሞክሮ ነው በዋናነት ጠቀሜታ ላይ የዋለው። የአኀት አብያተ ክርስቲያናት የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎቻቸውን እንዴት እንደሚያስተምሩ የሚያሳዩ ልምዶች በተገቢ ሁኔታ ተወስደዋል። ይህ ከእኛ ቤተ ክርስቲያን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ለሥርዓተ ትምህርቱ ጥቅም ላይ ውሏል። በተለይ ከግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተወሰደው ልምድና ተሞክሮ በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ ሰፊ ድርሻ ይወስዳል።

# የነቢያት (የገና) ጾም

ምኒልክ ብርሃኑ

ልጆች እንደምን አላችሁ? እንደምን ከረማችሁ? አሜን! የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን፤ እኛ በጣም ደኅና ነን:: በቤተ ክርስቲያናችን አሁን ያለንበት ጊዜ የጾም ወቅት ነው:: የሚጾመው ጾም ደግሞ የነቢያት ጾም ወይም የገና ጾም ይባላል:: ይህንን ጾም ሁሉም ክርስቲያን ሊጾመው የሚገባው ታላቅ ጾም ነው::

ታዲያ ልጆች! እናንተስ ይህንን የገናን ጾም እየጾማችሁ ነው? …… እየጾማችሁ ከሆነ በጣም ጎበዞች ናችሁ! መጾም ደግሞ ክርስቲያናዊ ግዴታ በመሆኑ ሁላችንም ልጾም እና ልንጸልይ ይገባናል:: እንዲህ ካደረገን አምላካችን እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር ይኖራል ማለት ነው::

ልጆች! ጾም ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? …… እስኪ ለጓደኞቻችሁ፣ ለወላጆቻችሁ ስለ ጾም የምታውቁትን በሙሉ ንገሩዋቸው…… ጎበዞች::

ልጆች! ጾም ‹‹ጾመ›› ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲኾን፤ ትርጕሙም መተው፣ መጠበቅ፣ መከልከል ማለት ነው:: የምንከለከለው፣ የምንቆጠበው አንደኛ፣ ለተወሰነ ጊዜያት ከምግብና ከውኃ እንዲሁም ከሥጋ፣ ከእንቁላል፣ ከወተት፣ ከአሳ፣ በአጠቃላይ ከእንስሳት ተዋጽኦ ምግቦች ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ክፉ ነገር ከመሥራት፣ መጥፎ ነገር ከመናገር፣ እግዚአብሔር አታድርጉ ያለውን ከማድረግ ወደ ክፉ ሥፍራ ከመሄድ እንከለከላለን ማለት ነው::

ጾም በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን የታወቀ፣ በነቢያት የነበረ እና በሐዋርያት የተሰበከ ነው:: እንዲሁም ፈጣሪን መለመኛ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው:: በተጨማሪም ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ የተሰጠ የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው::

### እግዚአብሔር ስለጾም እንዳስተማረን፤

ልጆች! ስለጾም ያስተማረን ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር ነው:: በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን ገና በገነት ሳሉ “ከተፈቀዳላችሁ በስተቀር ሁሉንም አትብሉ” ብሎ መጾም እንዳለባቸው አስተምሯቸዋል:: (ዘፍ፪.፲፮-፲፯) እንዲሁም ጌታችን መድኃታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንጦስ አርባ ቀን እና አርባ ሌሊት ጾሞ አሳይቶናል ማለት ነው:: ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች መጾም እንዳለብን በተግባር አምላካችን ያስተማረን በመሆኑ ልንጾም ይገባል ማለት ነው::

### የጾም ጥቅም፤

ልጆች! ጾም ለመንፈሳዊ ሕይወት እጅግ ጠቀሜታ አለው:: ቅዱሳን አባቶቻችን በኑሮአቸው ሁሉ በጾም ሕይወት እየኖሩ እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ጠብቋቸዋል:: ስለዚህ እኛም እንደ እነርሱ ከክፉ ነገር እንድንጠበቅ መጾም አለብን:: በመጾማችን ደግሞ በኃጢአት ከሚመጣ ቁጣ እንድናለን፤ ከክፉ ነገር ሁሉ እንጠበቃለን:: ጾም ትህትናን፣ ታዛዥነትን ያስተምረናል:: ስለዚህ ልጆች እኛም እንደ

አባቶቻችን በሕይወታችን ሁሉ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዲኖር የጾም ሕይወት ሊኖረን ይገባል ማለት ነው፡፡

ልጆች! ስለጾም ይህን ያህል ከተነጋገርን አሁን ደግሞ ስለነቢያት ጾም እንማራለን፡፡ የነቢያት ጾም ምን እንደሆነ፣ ለምን እንደሚጾም፣ ከጾም የምናገኘው ጥቅም ምን እንደሆነ እንማራለን ማለት ነው፡፡ በጥሞና እንድትከታተሉ እየጋበዝን መልካም ንባብ እንመኛለን፡፡

## የነቢያት ወይም የገና ጾም

ልጆች! ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደምታስተምረን ጾም የግል እና የዐዋጅ አጽዋማት በመባል በሁለት ይመደባል፡፡ የዐዋጅ አጽዋማት የሚባሉት ደግሞ ሰባት ሲሆኑ፤ እነርሱም የነቢያት (የገና) ጾም፣ የዐቢይ ጾም፣ የፍልሰታ ጾም፣ የነነዌ ጾም፣ የገሀድ ጾም፣ የድኅነት ጾም (ረቡዕ እና ዐርብ) እና የሐዋርያት (የሰኔ)ጾም ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ደግሞ እነዚህን አጽዋማት ሁሉም ክርስቲያን መጾም እንዳለበት ትእዛዝ ሰጥታለች፡፡ ስለዚህ የነቢያት ወይም የገና ከሰባቱ የዐዋጅ አጽዋማት መካከል አንደኛው ማለት ነው፡፡

የነቢያት ጾም እኛ ክርስቲያኖች የምንጾምበት ምክንያት ቅዱሳን ነቢያት ጾመውት ስለነበር ነው፡፡ በየዘመናቱ የተነሡ ቅዱሳን ነቢያት እግዚአብሔር አምላካችን ዓለምን ለማዳን ከሰማያት ወርዶ፤ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፤ በመስቀልም ተሰቅሎ እንደሚያድነን አስቀደመው በትንቢት ተናግረው ነበር፡፡

ታዲያ ልጆች! እነዚያ ቅዱሳን ነቢያት ትንቢቱ ተፈጽሞ አምላካችን ከሰማይ ወርዶ፣ ከእመቤታችን ተወልዶ፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ዓለምን የሚያድንበትን ጊዜ ለመመልከት ስለፈለጉ ሁልጊዜ በጾም እና በጸሎት ተወስነው ይጠባበቁ ነበር፡፡ ከዚያም ከብዙ ጊዜ በኋላ ቀኑ እና ሰዓቱ ሲደርስ የነቢያቱ ትንቢት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ ፍጻሜ አግኝቷል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ልጆች! አባቶቻችን ይህንን ምስጢር በማሰብ እና እኛም እንደ ነቢያቱ መጾም ስላለብን ሥርዓት ሠርተውልናል ማለት ነው፡፡ ስያሜውን ቀድመው ነቢያት ስለጾሙት የነቢያት ጾም በማለት ሰይመውታል፡፡ የምንጾመው ደግሞ ሁል ጊዜ በየዓመቱ ከኅዳር ፲፭ ቀን ጀምሮ እስከ የገና በዓል ዋዜማ ድረስ ለአርባ ሦስት ቀናት ነው፡፡

ልጆች! አባቶቻችን ይህንን የነቢያት ጾም ጾመው በረከት አግኝተውበታል፡፡ እግዚአብሔርም ከብዙ መከራ እና ፈተና ጠብቆአቸዋል፡፡ እኛ እንደ እነርሱ በረከትን እናገኝ ዘንድ፣ አምላካችን ከችግር እና ከፈተና እንዲጠብቀን፣ ሀገራችንንም እንደሚጠብቅልን፣ ትምህርታችንንም እንዲገልጽን ይህንን ጾም ልንጾም ይገባል፡፡ ስንጾም ደግሞ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ሲል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን በማሰብ መሆን አለበት፡፡

በሉ ልጆች ለዛሬ በዚህ ይብቃን፡፡እግዚአብሔር አምላክ ጾሙን የበረከት ያድርግን፡፡በሰላም እንዳስጀመረን በሰላም ያስፈጽመን፡፡በሚቀጥለው ጊዜ በሌላ ርእስ ጉዳይ እስከምንገናኝ ደኅና ሁኑ፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ቅዱሳት ሥዕላቱ ይከበሩ!

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ኦርቶዶክሳዊ ክርስትናን ከሌሎች በክርስትና ስም ካሉ ቤተ እምነቶች ልዩና ጥንታዊ መሠረቱን ጠብቆ የመገኘቱ አንዱ ማሳያ በቅዱሳት ሥዕላት ላይ ያለው ትምህርትና እምነት ነው። ቅዱሳት ሥዕላት በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ በሥርዓት አምልኮ ሥፍራ ያላቸው ቅዱሳት ንዋያት ናቸው። የእግዚአብሔርን ሥራ ዘወትር በማሰብ የቅዱሳን ሥራ፣ ተጋድሎ፣ ተአምር፣ ትምህርት የምንዘክርባቸው ቅዱሳት ንዋያት ናቸው።ያን ባደረግን ጊዜ ሁሉ ከእግዚአብሔር ረድኤት ከቅዱሳኑም በረከት የምንሳተፍበት ነውና።

ቅዱሳት ሥዕላት በዚህ ደረጃ በክርስትና ሕይወታችን ውስጥ ቦታ እንዲኖራቸው ግን በሥርዓት መሣል አለባቸው። ቅዱሳት ሥዕላት በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ የራሳቸው አሣሣል ባህል ትውፊት አላቸው።ከዚያ ሲያፈነግጡ ወደ ስሕተት ሊጥሉና ላልተፈለገ ፈተና ሊዳርጉ ይችላሉ።

ከሁሉም በላይ መታወቅ ያለበት ግን በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ ‹‹እገሌን ይመስላሉ›› የማይባሉ ትእምርታዊ/ ተምሳሌታዊ /Symbolic/ ሆነው የተሠሩ መሆን አለባቸው። በቀለማቸው፣ የሰውነት አካላት አሣሣላቸው፣ አቀማመጣቸው፣ ምጣኔያቸው፣ የአለባበስ ገጽታቸው....የራሱ ምሳሌያዊ ዋጋ አለው።በሥዕሉ ላይ ቅዱሱን ክርኰሱ፣ የምንለየው አንዱን ቅዱስ ከሌላው የምንለየው፣ የጌታን ከሐዋርያት፣ ሰዎችን ከመላእክት፣ ቅዱሳን መላእክትን ከክፉ መናፍስት የምንለየው የታወቀ አንድ መልክ በመስጠት ሳይሆን በሥዕሉ በሚገለጸው ድርጊት፣ ወይም ማን መሆናቸውን ለማመልከት በምንጠቀምባቸው ምልክቶች፣ ቀለሞች፣ የአካላዊ ቅርጽ አቀማመጦች ወዘተ ነው። ለምሳሌ ለመላእክት ክንፍ ስላላቸው ከሰዎች እንለያለን፤ ቅዱሳን ሁለት ዐይን ሆነው በመሣላቸው አንድ ዓይና ሆነው ከሚሣሉ ከክፉዎች እንለያለን፤ቅዱሱን አክሊለ ብርሃን በማድረግ ከሌሎች እንለያለን። አንዱን ቅዱስ ከሌላው የምንለየው ከተአምሩ ከገድሉ የምናውቀውን የታወቀ ተግባር/ድርጊት/ በማሳየት ሊሆንም ይችላል።

አንድ ዓይነት የፊት ገጽታ ያላቸው ቅዱሳን በሚሠሩት ድርጊት/ባላቸው ምልክት/ ማን እንደሆኑ ለያይተን እናስባቸዋለን። ቅዱስ ጴጥሮስ ቁልቁል ከተሰቀለበት መስቀሉ ጋር ካሳየነው ጳውሎስን ደግሞ ከተሰየፈበት ሰይፍ ጋር ስለምናሳየው ማንነታቸውን ለይተን እናውቃቸዋለን። ቅዱስ ጴጥሮስን በሚይዘው መክፈቻ ቁልፍ ሲሣል ጳውሎስን በጻፋቸው መልእክታት ወይም በደማስቆ መንገድ በታየው ራዕይ እንገልጸዋለን። ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስን ከፈረሱ ጋር ስናሳየው ሰማዕቱ እስጢፋኖስ ደግሞ ድንጋይ ከያዙ ወጋሪዎቹ ፊት እየጸለየ በማሳየት እንለየዋለን። ይህንና ይህን በመሰለ መንገድ እንለያለን እንጂ በዚህ ዓለም እንዳለ ሥዕል፣ ፎቶ የአንዱን መልከ መልካም የአንዱን መልከ ጥፉ የአንዱን ፀጉር ጨብራራ የሌላው ዞማ እያደረግን በዚህ ዓለም ባሉ ሰዎች ገጽታ የታወቀ አንድ መልክ ይዘን የምንለየው አይደለም። ይህ ምልክታዊ አሣሣል በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ ሥርዐት ሆኖ ተጠብቆላቸው የተሠሩትን ለሕይወታችን መጠቀም ይገባናል።

ከዚህ አንጻር ሲታይ ግን በበርካታ ምእመናን ዘንድ ቅዱሳት ሥዕላትን መርጠን ለመጠቀም የሚታይብን ስንፍና ትዝብት ላይ የሚጥል ነው። በገበያ የተገኘውን ሁሉ ገዝቶ ለአገልግሎት ለማዋል መሞከር ከኦርቶዶክሳዊ እምነት ሥርዓት ውጪ መሆንን አስከትሏል። ኦርቶዶክሳዊ ሥዕሎች ምን ዓይነት ናቸው ብሎ ለመጠየቅ ከመስነፍ ጀምሮ ገዝቶ ለቤተሰብ እና ለአብያተ ክርስቲያት አገልግሎት ለመስጠት የሚኬድበት መንገድ ነገሮችን እያወሳሰበ ነው።

በርካታ በሮማ ካቶሊክ የአሣሣል መንገድ የተሣሉ ከትእምርታዊነት ያፈነገጡ ‹‹እገሌን ይመስላሉ›› የሚባሉ /realistic/ ሆነው የተሣሉ ሥዕሎችን ገዝተን ስንጠቀም ይስተዋላል። እውናዊ ሥዕሎች በዚህ ዓለም ካሉ ሰዎች ‹‹የእገሌን መልክ ይመስላል›› ብለን እስክንል ድረስ የፎቶ ያህል ለዚህ ዓለም የቀረቡ ሥዕሎች ናቸው።

ሌላው ለትዝብት የሚዳርገው ከቅዱሳት ሥዕላት ጋር የተያያዘ አጠቃቀም ነው። ቅዱሳት ሥዕላት አስባርከን ልንጠቀምባቸው ሲገባ ከገበያ ገዝተን በፈለግነው መንገድ ለመጠቀም መሞከር ሥርዓትን ያዛባል። የምንፈልገውንም መንፈሳዊ በረከትና

ኃይል እንድናገኝ ሥዕላት መባረክ አለባቸው፡፡

እንዲሁም መንፈሳዊ ጥቅም ለማግኘት የወሰድናቸውን ሥዕላት በክብር ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ምእመናን ለቅዱሱ ያላቸውን ፍቅር የገለጹ እየመሰላቸው ሥዕሉን አላግባብ በየሥፍራው ማስቀመጥ መለጠፍ ያዘወትራሉ፡፡ሥዕላት ግን ለእነርሱ ክብር ተብሎ በተለዩ ቦታዎች መቀመጥ አለባቸው፡፡የተለየ የጸሎት ቤት ያላቸው ምእመናን ከሌላ ዓለማዊ ነገር ጋር ሳያገናኙ በክብር ለማስቀመጥ ይቻላቸዋል፡፡ካልሆነ ደግሞ ሥዕላት የሚቀመጡበትን የቤታችንን ክፍል ለየት አድርጎ ሌሎችን ነገሮች ከዚያ አርቆ በማስቀመጥ አክብሮታችንን መግለጽ እንችላለን፡፡ ስንጸልይ ወደ እነርሱ ዞረን በተመስጦ ለመጸለይ ያስችለናል፡፡ሥዕላት ከዓለማዊ ሥዕሎች፣ ከወገን ከዘመድ ፎቶግራፎች ጋር በአንድ ላይ እንዲቀመጡ ማድረግ ለቅዱሳት ሥዕላት ያለንን ክብር ያሳንሳል፡፡ ፍቅራችንንም ያጎድላል፡፡

ሌላው በቅዱሳት ሥዕላት አያያዝ ላይ ያለው ችግር ሥዕሎች አቧራ እንዲጠግቡ፣ ለመቀደድ ለመሰበር የተጋለጡ እንዲሆኑ ማድረግ ከሥርዓት መውጣት ነው፡፡ከዚያም አልፎ ቅዱሳት ሥዕላት በአግባቡ ባለመያዛቸው ምክንያት ቀለማቸው ደብዝዞ፣ ታጥፈው ተጨማደው የሚታዩባቸው ቤቶች ካሉ መታረም ያለባቸው ቤቶች ናቸው፡፡

ቅዱሳት ሥዕላትን በአግባቡ በማይያዙበት መንገድም ከማስታወቂያ፣ ከፖስተሮች፣ ከቢል ቦርዶች፣ ከበራሪ ወረቀቶች ጋር በማተም በየሜዳው ማራከስ፣ ለመረጋገጥና ለመቀደድ እንዲጋለጡ ማድረግ ሌላው ዘወትር የምንታዘበው ድርጊት ነው፡፡በታክሲዎች፣ በአጭርና ረጅም ርቀት የትራንስፖርት መገልገያዎች ውስጥም ቅዱሳት ሥዕላት ከሌሎች ዓለማዊ ምናልባትም በእጅጉ ከመንፈሳዊ ሕይወታችን ጋር ከሚቃረኑ ምስሎች ጋር ተዳብለው ሲቀመጡ ስናይ የሚያስተዛዝበን ኖኗል፡፡

ቅዱሳት ሥዕላት ቅዱሱን እንድናስብ እንድንዘክር፣ እንድናከብር የሚያስታውሱን በቁስ ላይ የተሠሩ በመሆኑ የተሠሩበት ቁስ በዕድሜ ብዛት፣ በሚደርስበት ጉዳት ወዘተ የቅዱሳት ሥዕላቱን አገልግሎት ማብቂያ ላይ ካደረሰ በሥርዓቱ መሠረት ማደስ፣ መለወጥ ወይም ማንሣት ሲገባ በቤታችን አንዳንዴም በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያት አካባቢም እንዳሉ እንዲቆዩ ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ሲያረጁ ፈርሰው እንደሚሠሩ፣ በርካታ ንዋየ ቅድሳት ሥርዓቱን ጠብቀው በአዲስ እንደሚተኩ ቅዱሳት ሥዕላትም በአዲስ መተካት አለባቸው፡፡

ቅዱሳት ሥዕላት በሕንጻ አብያተ ክርስቲያት ውስጥ የሚሣሉበት፣ የሚቀመጡበት የየራሳቸው ሥፍራ አላቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ የሥላሴ ሥዕል፣ ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል የሚሣልበት ሥፍራ፣ የሰማዕታት የሚሣልበት ሥፍራ፣ የሐዋርያት ሥዕል፣ የነቢያት ወዘተ የሚሣልበት በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት በየትኛው የቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳ በየትኛው አቅጣጫ የሚለውን ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን የሚነግረን ነው፡፡ አሁን አሁን ግን ይህ ሥርዓት የፈረሰ ይመስል ምእመናን የሚፈልጉትን ሥዕል በሸራ፣ በመስተዋት፣ በወረቀት፣ በሰፊው ወይም በጠባቡ እያሣሉ ባገኙበት ሥፍራ ሲያስቀምጡ የሚመክር፣ የሚያስተምር መጥፋቱ ሥርዓቱ መደበላለቅ ውስጥ እንዲገባ የሚያስገድድ ነው፡፡

ሌላው አስተዛዛቢ ነገር ቅዱሳት ሥዕላትን በልብሶቻችን ላይ አሥለን ለብሰን ለመዞር መሞከርም ሊያስነቅፍ የሚችል ነው፡፡ ልብሶቻችን በማደፍና በመቀደድ ስለሚጎዱ አብሮ ሥዕሉ ክብር እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም ምእመናንን ትዝብት ላይ የሚጥለው ነገር ቅዱሳት ሥዕላትን ለንግድ ዓላማቸው በማይገባ መንገድ ለሚጠቀሙ ወገኖች መሣሪያና ተባባሪ የመሆን ነገር ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ቅዱሳት ሥዕላትን ክብር በሚያሳጣ መንገድ ከመጠቀም እንዲቆጠቡ ምርትና አገልግሎታቸውን ባለመቀበል ከእነርሱ ጋር ባለመገበያየት ወይም ለዓላማዎቻቸው ሁሉ አዎንታዊ ምላሽ ባለመስጠት ሥርዓትን ማስከበር፤ ቤተ ክርስቲያን ማክበር ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ምእመናን ስለቅዱሳት ሥዕላት ምንነት በሚገባ ማወቅ፣ የአጠቃቀም ሥርዓታቸውን መረዳትና ማክበር፣ ሥርዓቱን ከሚያጠፉና የቅዱሳኑን ክብር ከሚያሳጡ አካሄዶች ሁሉ መራቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ካልተበቀልኩ ዕረፍት የማገኝ አይመስለኝም

***ክፍል አንድ***

ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን ሰነበታችሁ? ስሜ አምኃ ሥላሴ ይባላል የ፳፮ ዓመት ወጣት ነኝ። ታናሼ የሆነች አንዲት እኅት አለችኝ፤ ተምራ ለወግ ለመዓርግ ለመብቃት ብዙ ሕልም ነበራት። ከዕለታት በአንዱ ቀን ግን በገጠማት ችግር ምክንያት ዛሬ ላይ ሕይወቷ ተመሰቃቅሏል። እኅቴ አብረውን ከኖሩ መልካም ጎረቤቶቻችን ቤት በሚኖር ጎረምሳ ሳታስበው ተደፍራለች። በዚህ ነገር ልቤ ተነክቷል። እኔም እኅቴን ከእንዲህ ዓይነት ነገር መታደግ ባለመቻሌ በቀንም በሌትም ቁጭት ይሰማኛል።። እርሷን ቤተሰቡ ሁሉ ለማረጋጋት ቢሞክርም በእኔ በኩል ግን እስከ አሁን ከብስጭት፣ ከቁጭት ልወጣ አልቻልኩም። በእኔ በኩል ዕረፍት የማገኝ የሚመስለኝ የበደላትን ሰው ከተሰወረበት አግኝቼ ስበቀለው ነው። እንዲህ ዓይነት ጨካኞች ከምድር ላይ በጭካኔ ካልተወገዱ ዕረፍት አይገኝም ብዬ አስባለሁ። በሌላ በኩል ከዚህ ስሜት ለመውጣት ጥረት ባደርግም እኅቴን ባየኋት ቁጥር እበሳጫለሁ። ምን ትመክሩኛላችሁ።

ውድ ጠቂያችን በእኅትዎ ላይ የደረሰው የአካልና የስሜት ጉዳት በጣም የሚያሳዝን ነው። በዚያም የተነሣ በእርስዎም ላይ የተከሰተው ብስጭት የሚጠበቅ ነው። ። ነገር ግን ከዚህ ስሜት ለመውጣት አለመቻልዎና ሌላ ፈታኝ መንፈስ እንደከበበዎ በማስተዋል እንዴት ላድርግ ብለው ከጋዜጣችን ዓምድ መንፈሳዊ ምክርን ለማግኘት መሻትዎ መልካም ነው።

ሴት እኅቶቻችን ሰይጣናዊ በሆነ መንፈስ ተገፋፍተው ለክፉ ሥራ በሚነሣሡ ሰዎች ምክንያት ተገደው የሚደፈሩበት ሁኔታ በሀገርም ይሁን በዓለም ላይ አሳሳቢ ከሚባሉና እግዚአብሔር ከሚያዝንባቸው የሰዎች አሳፋሪ ድርጊት አንዱና ዋነኛው ሆኖ መቀጠሉን እያየን ነው። ይህ ነገር በእርስዎ እኅት ላይ ለዚያውም በሚታመን ወዳጅ ጎረቤት በሚኖር ጎረምሳ መፈጸሙ በእኅትዎ ላይ የሚያደርሰው ዘርፈ ብዙ ተጽእኖ ከባድ ነው።

እንዲህ ዓይነት ነገር በተለይ በክርስቲያን መንፈስ ንጽሕናቸውን ጠብቀው በሚመርጡት ሕይወት ለመኖር ራሳቸውን በመልካም አኗኗር እያዘጋጁ በሚኖሩ እኅቶቻችን ላይ ሲሆን ደግሞ የበለጠ ያማል። እኅታችን ተምራ ሠርታ ለወግ ለመዓርግ መብቃትን ስትናፍቅ በደረሰባት የአካል ጉዳትና የስሜት ስብራት አንገቷን ስትደፋ፣ስታዝን፣ ስታለቅስ ማየት እንኳን ለቤተሰብ፣ እንኳን አብሮ ላለ ወንድም ለሌላውም በቅርበት ለሚያውቅና የኃጢአቱን/የወንጀሉን/ አስከፊነት ለሚረዳ ወገን ሁሉ አሳዛኝ ነው።

ጠያቂያችን ሊገነዘቡት የሚገባው ትልቁ ጉዳይ ከእርስዎ የቁጣ ስሜት በላይ ቅድሚያ መሰጠት ያለበት የጉዳቱ ቀጥተኛ ሰለባ የደረሰባትን እኅትዎን ሁለንተናዊ ጉዳት ለመጠገን መፍትሔዎችን ማፈላለግ ላይ ነው። ስለዚህም ሌላው የቤተሰብ አባላት ከእኅትዎን ጎን በመሆን ለማረጋጋት ርምጃ ቢወሰድና የተሰበረውን ሕሊናዋን ለመጠገን የማዝናናትና ተመሳሳይ ሁለንተናን በሚፈውስ ዓይነት ብዙ መፍትሔ ልጅቷ እንድታገግም ማድረግ ይገባል።

ለዚህም የደረሰባትን አካላዊ ጉዳት ለውስብስብ የጤና እጦት እንዳይዳርጋት በሕክምና እንድትጎበኝ ከማድረግ ጀምሮ በመንፈስ እንድትጽናና፣ በስሜትም እንድትረጋጋ የሚያደርግ መፍትሔን ለማቅረብ በቅድሚያ ቢንቀሳቀሱ የበለጠ እኅትዎን ይጠቅማሉ። ለዚህም በቃለ እግዚአብሔር ወደሚያጽናኑ አባቶች ካህናት፣ መምህራነ ወንጌል፣ በጸሎት ወደሚያግዙ ገዳማውያን ማቅረብና በቅዱስ ቃሉ በጽናት እንድትቆም ማድረግ ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ቃል ኃይል ያለው ቃል ነው፤ የሚፈውስ ቃል ነው። ያዘኑትን የሚያረጋጋ፣ ተስፋም የሚሰጥ ቃል ነው። ለጉዳት ለኀዘን የሚዳርግ የዚህን ዓለም ነገር ሁሉ የምናይበትን መነጽር የሚያስተካክል በመሆኑ እኅትዎ የደረሰባትን ጉዳት እንዴት አድርጋ ልትረሳው እንድምትችል መንገድን ሁሉ የሚያመላክት ነው።።

ከዚህ በተጨማሪ ‹‹ያዘነ ቢኖር ይጸልይ›› እንደተባለ በጸሎት ሐዘኗን እንድትገልጽ፣ በጸበሉ በእምነቱ ለሥጋም ለነፍስም ጽናትና ኃይልን እንድታገኝ በሚያረጋጋ ስፍራ በሱባኤ ማቆየትም ሌላው ወሳኝ መንፈሳዊ እርምጃ ነው። በመከራ በስቃይ በችግር በፈተና ውስጥ ያለፉ የደጋግ ጻድቃንን ሕይወት የምትሰማበት፣ ስለሕይወታቸው የተጻፉ ነገሮችን

የምታነብበት ሁኔታንም ማግቻቸት ከእርስዎ ይጠበቃል።

ሌላው ጠያቂያችን ትኩረት የሰጡት ነገር በእርስዎ ውስጥ ስለሚንቀለቀል የበቀል መንፈስ ነው። በእርስዎ ውስጥ የሚመላለሰው የበቀል መንፈስ መንሥኤም እኅትዎን ከዚህ የመደፈር አደጋ መጠበቅ ያለመቻል፣ እንዲህ ያሉ ስሜቶች በሚሰሙን ጊዜ የደፈረንን በመድፈር፣ የበደለንን ራሳችን በመቅጣት፣ ወይም የጎዳንን ከዚህ ዓለም በማጥፋት ዕረፍት የምናገኝ ይመስለናል።

ውድ ጠያቂያችን በውስጥዎ የሚታገልዎ የአለማድረግ ስሜትም በውስጥዎ ያለ መልካም መንፈስ ወደ ስሕተት እንዳይወድቁ የሚሰጥዎ ረቂቅ ምክር መሆኑን መገንዘብ አለብዎ። ወደ እኛም ጋዜጣ ምን ላድርግ ብለው ለመጻፍ ያስገደደዎ ነገሩ በክርስትናው ዓለም ብዙ የሚያጽናና ትምህርትና ቀኖና መኖሩን በመረዳትዎ ነው።

የበቀል መንፈስ ጎጂና የማይገባ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል። የክርስትና እምነት ዋነኛ መርኆም የበደሉን ይቅር ማለት መሆኑ ግልጽ ነው። እርስዎም ከዚህ የመንፈስ ግልቢያ ለመላቀቅ እንዲችሉ ውስጥዎ የሚነግርዎትን ምክር በቃለ እግዚአብሔር ማጉላትና በትዕግስት ማድረግ ከሚገባዎ አልፈው እንዳይሄዱ መጠንቀቅ ነው።

በእኅትዎ ላይ የደረሰውን ጉዳት በወንጀልነቱ መረጃና ማስረጃን አቅርቦ በዚህ ዓለም ሥርዓት ሀገርና መንግሥት በሚያስቀምጡት አሠራር አጥፊውን ማስቀጣት የሚገባ ነው። ይህንንም የሚከለክል ነገር አይኖርም። በአጥፊው ላይ የሚደርሰውም ቅጣት ከእርስዎ የሚመነጭ ሳይሆን በሚኖርብን ሀገርና ሕዝብ ውስጥ ካለው የስምምነት ሕግ የመነጨ ለጥፋቱ የተቀመጠ ቅጣት ነው። ለምሳሌ በወንጀል ሕግ መቅጫ ፮፻፳(፩) ‹‹ማንም ሰው የኃይል ድርጊት በመጠቀም ወይም በብርቱ ዛቻ ወይም ኅሊናዋን እንድትስት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ መከላከል እንዳትችል በማድረግ ከጋብቻ ውጪ አስገድዶ ከአንዲት ሴት ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት የፈጸመ እንደሆነ ከአምስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል›› ይላል። የቅጣት ደረጃው ይህ ብቻ ሳይሆን እንደ ወንጀሉ ዓይነት፣ ክብደት እና ቅለት በቀጣይ ንዑስ አንቀጽ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ሁኔታ በመዘርዘር ቅጣቱን ያስቀምጣል። በመሆኑም በዚያ ልክ አጥፊው ቅጣቱን መቀበል የሚገባ ነው።።

ከዚያ በመለስ ግን በውስጣችን የሚታገለንን የበቀልና የቁጣ መንፈስ በቃለ እግዚአብሔር ማብረድ ለክርስቲያን የሚገባ ነው። ክርስቲያን በተበደለው ልክ የማይበድል፣ የበደሉትንም ይቅር የሚል እንዲሆን በጥምቀቱ የተቀበለው ቃል ኪዳን ነው። ይህም ክርስቶሳዊ ከሆነው ፍጹም ፍቅር የመነጨ ነው። ክርስቶስ በደለኞችና ጠላቱ ሰንሆን ራሱን እስከመስጠት የደረሰ ፍቅሩን ለእኛ እስኪገልጽ የታገሰን ትዕግስትና ያደረገልንን ቸርነት የክርስትና እምነታችን መሠረት ነው። ስለዚህ ከዚህ ሕይወት መሠረት ያፈነገጠ እርምጃ ሁሉ ከክርስቲያናዊ መንፈስ የወጣ በመሆኑ ሊበረታታ አይችልም።

ከዚህ በተጨማሪ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠላቶቻችንን እንድንወድ እንዳንበቀልም‹‹ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ፣ ጠላታችሁን ውደዱ፣ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ፣ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፣ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ። . . . .›› (ሉቃ.፮፥፳፯–፴፮) በማለት በቅዱስ ወንጌሉ ያወጀልን ጉዳይ በመሆኑ በውስጣችን ያለውን የሥጋ ቁጣ በቃሉ ለማብረድ እንገደዳለን፤ ጌታችን ‹‹ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል።እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤ እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት፤ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ። ለሚለምንህ ስጥ፥ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል። ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?›› (ማቴ ፭፥ ፴፰-፵፮) ብሏልና፡።